በ ደ.ብ.ብ. ህ. ክ.መ
የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

# በክልሉ የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የህዝብ ንቅናቄ ውስጥ መንግሰታዊ ያልሆኑ አካላት ያላቸው የጎላ ድርሻና የሚጠበቅባቸው ሥር ነቀል ሁለንተናዊ ለውጥ

**«የውይይት መነሻ ሀሳብ»**

**ግንቦት** 1996 **ዓ.ም**
**አዋሳ**

# 1. <u>መግቢያ</u>

መንግስት ለህ/ሰቡ ልማት፣ ጤናማ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዞታ፣ ሰላምና ፍትህ፣.. መረጋገጥ የገባውን ቃል እውን ለማድረግ የሚያወጣቸውን መርህ ግብሮች የሚያስፈጽሙ መንግስታዊ ተቋማት አሉ፡፡ እነዚህ ተቋማት በቀጥታ በመንግስት በጀት ይንቀሳቀሳሉ፡ የመንግስት ፖሊሲ ያስፈጽማሉ፡፡

ከነዚህም ውጪ የመንግሰት የልማት፣ ፍትህና ደህንነት አጋር ሆነው ለህ/ሰቡ በረካታ አገልግሎቶችን የሚሰጡ በአገሪቱ ደንብና ህግ ስር የራሳቸውን ተልዕኮ ካለ መንግስት ጣቃ ገብነት የሚከናወኑ አካላትም አሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉት አካላት በአጠቃላይ “መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት” ናቸው፡፡ ዜጎች በግልና በጋራ ሆነው የአባልነት መዋጮ፣ የጉልበትና መሰል ነፃ አገልግሎት፣.. አሰተዋጽኦ እያደረጉ የሚያንቀሳቅሷቸው አልያም ትርፍ ለማግኘት ሲሉ ያቋቋሙዋቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ አገር ተደራጅተው እዚህ ክልል ውስጥ የሚሰሩም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ እንደነዚህ ያሉት ተቋማት ለአንድ አገር ልማት፣ ማህበራዊና ፖለቲዊ መረጋጋት የሚያበረክቱት አሰተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡

አብዛኛዎቹ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት መዋናነት በሰብአዊና ህብረተሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ዙሪያ ተሰልፈው መንግስትን እያገዙ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ አካላት ከተሰለፉባቸው የህብረተሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች አንዱ ደግሞ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ክልላችን የሚያከናውነው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ በዘርፈ ብዙ ምላሽ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ተሰልፈው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው፡፡

እነዚህ አካላት ከዚህ በፊት ይታዩ የነበሩ የአስተሳሰብ አሰራርና አደረጃጀት ችግር በመቅረፍ ለበለጠ ውጤታማ የፀረ- ኤድስ ስራ መሰለፍ፣ ክልሉ ላወጣው ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ስኬታማነት አይነተኛ አጋዥ በመሆኑ እነዚህ የእንቅስቃሴ አጋሮች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መመልከቱ አስፈልጓል፡፡

# 2. “መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት” እነማን ናቸው ?

በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠር ዙሪያ ከሚኖራቸው ድርሻ ካላቸው አደረጃጀትና ለዚህ ሰነድ አጠቃቀም እንዲያመች መንግስታዊ ያልሆነውን ተቋማዊ ዘርፍ በሚከተሉት ሰባት ንዑስ ዘርፎች እንከፈላቸዋለን። እነዚህም

ሀ. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /NGOs/
ለ. ሲቪል ማህበራት /CSOs/
ሐ. የብሄረሰብ የልማት ማህበራት
መ. ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት /CBOs
ሠ. ልማታዊ አትራፊ ተቋማት
ረ. የሀይማኖት ተቋማት
ሰ. የግል ተቋማት /POs/
ሽ. ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ሚኖሩ ዜጎች ማህበራት

ሀ. *__መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /NGOs/__*

በሎጂክ ደረጃ ከላይ ከሀ-ሰ የተዘረዘሩት ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ናቸው። ሆኖም ግን በተለመደው የአገራችን አሰራር/በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን እና በክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ አተረጓጎም/ በዚህ ስም የሚጠሩ የተለዩ መንግሰታዊ ያልሆኑ ተቋማት አሉ።

በመሆኑም በዚህ ሰነድ " መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች " ያልናቸው እነዚህ ከላይ በተጠቀሱት መ/ቤቶች በዚህ ስም የተመዘገቡ በመግባረ-ሰናይ በማህበረሰብ አቀፍ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት የተሰማሩ አትራፊ ያልሆኑ የፖለቲካ ፣ የእምነት ወዘተ ወገንተኛነት የሌላቸውን አካላት ነው።

እነዚህ ድርጅቶች አገር በቀል /Local/ እና አለምቀፍ /International/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ።

አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቁጥራቸው እየተበራከተ የመጣና በዜጎች በጎ ፈቃደኝነት ለሰብዓዊና ልማታዊ የህብረተሰብ አገልግሎቶች በአገር ውስጥ የተቋቋሙ አትራፊ ያልሆኑ ደርጅቶች ሲሆኑ አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ምስረታቸው ከኢትዮጲያ ወጪ የተቋቋሙና ተመሳሳይ የምግባረ ሰናይና የማህበረሰብ ልማት ስራን ለመስራት ከፌደራል ፍትህ ቢሮ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። እነዚህ ደርጅቶች አንዳንዶቹ ራሳቸው በፈፃሚነት እየተሳተፉ ያሉ ከፊሎቹ ሌሎች ፈፃሚ አካላትን በቴክኒክና በፋይናንስ የሚደገፉ የተቀሩት ደግሞ በሁለቱም አይነት ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ የተሰማሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ለ. ብዙሀን ማህበራት /Civil Society Organization/**

ሲቪል ማህበራት የፖለቲካ ፓርቲ /ቡድን/ ሳይሆኑ ለህብረተሰባቸው በአጠቃላይ ለሚወክሉት የህ/ሰብ ክፍል በተለይ ኢኮኖሚዊ፣ ማህበራዊና ሰብአዊ ደህንነትና እድገት የሚበጅ አስተዋጽኦ ለማበርከት በነፃ ፈቃድ የተሰባሰቡ ዜጎች ጥምረቶች ናቸው::

ሲቪል ማህበራት ሙያን፣ፆታን፣እድሜን፣ የሥራ ሁኔታን፣ ወዘተ መሰረት አድርገው ሊቋቋሙ ይችላሉ:: በአብዛኛው ተመሳሳይ ፍላጎት፣ አጀንዳ፣ ባህሪይ፣ ወዘተ ያላቸው በርካታ የህ/ሰብ ክፍልን የሚወክሉ ናቸው:: ሰፊ ህዝባዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት አላቸው በፌደራል ወይም የክልል ፍትህ መስሪያ ቤቶች ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ናቸው::

የሴቶች ማህበራት ፣ የወጣቶች፣ የመምህራን፣ የሰራተኞች፣ የአገልግሎት የህብረት ስራ፣ የአሰሪዎች፣ የነጋዴዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ ወዘተ ማህበራት በዚህ ዘርፍ ከሚካተቱት ውስጥ አንዳንዶቹ ናቸው::

### ሐ. የብሄረሰብ/ የዞን/ክልል/ የልማት ማህበራት

በተለይ ከክልላችን እውነታ አንፃር ስናየው ከፍተኛ የልማት ድርሻ ከሚኖራቸው ሀይሎች ዋነኛዎቹ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የተደራጁ የልማት ማህበራት ናቸው:: እነዚህም ከፌደራል ወይም ክልል ፍትህ አካላት ፈቃድ የሚሰጣቸውና አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ካልናቸው ጋር ተመሳሳይ ሚና ያላቸው ናቸው:: እነዚህን ልዩ የሚያደርጋቸው የሚወክሉት ማ/ሰብ ቋንቋ፣ የባህል፣ ወግና እምነት በሚጋሩ የራሱ የህ/ሰቡ አካላት የተመሰረቱና የሚንቀሳቀሱ እስከታችኛው የህ/ሰብ እርከን የሚዘልቅ አደረጃጀት ያላቸው መሆኑ ነው::

በአሁኑ ሰዓት በኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ያሉት እንደወላይታ፣ ከፋ፣ጉራጌ፣የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች እና መሰል የልማት ማህበራት ከነዚሁ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው::

### መ. ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት /Community Based Organizations/

እነዚህ የማህበረሰቡ አካል የሆኑና በአንድ አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የእለት ተእለት የጋራ ጉዳዮቻቸውን በጋራ የሚያስፈጽሙበት፣ የሚፈቱበት፣ የሚመክሩበት .. አካባቢያዊ ተቋማት ናቸው:: በተለያየ መልኩ እነዚህ ተቋማት በዚያ ህ/ሰብ ውስጥ ተሰሚነታቸው ከፍተኛ ነው ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ሀይማኖታዊና መሰል የማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ::

እድሮች የወጣት ክበባት፣የሴቶችና ቡድኖች ወዘተ ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት በሚል የሚጠቀሱ ናቸው:: በየሰፈሩና ቀዬው በረካታ እነዚህን መሰል የማህበረሰብ ተቋማት አሉ::

### ሠ. አትራፊ የልማት ተቋማት

በአሁኑ ሰዓት በተለይ ከተፈጠረው አመቺ የኦንቨስትመንት እድል በተያያዘ በክልላችን ትላልቅ የሆኑ የኢንቨስትመንት ተቋማት እየተስፋፉ ነው:: ቀደም ሲል በመንግስት ቀጥታ ባለቤትነት ይንቀሳቀሱ የነበሩ አትራፊ የንግድ ማዕከላትም አሁን ራሳቸውን ችለው በነፃ ገበያው ስርዓት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ተደርጎ ይገኛል::

በተለይ ክልላችንን ስናይ በአሁኑ ሰዓት በርካታ የጉልበት ሰራተኞችንና ባለሙያዎችን አቅፈው የሚገኙ ትላልቅ ፋብሪካዎች፣ ሰፋፊ የቡና፣ ሻይ ቅጠልና ቅመማ ቅመም እርሻዎች እየተስፈፉ ነው:: እነዚህ በተለይ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ አንፃር ካላቸው ወሳኝ ሚናና ተጋላጭነት አኳያ ልዩ ትኩረት የሚሹ ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ናቸው::

አትራፊ የልማት ተቋማት በግል ባለ ሀብቶች ፣ አልያም በመንግስት የልማት ተቋማት ተቆጣጣሪ አካል ስር የሚተዳደሩ ሊሆኑ ይችላሉ:: ዋና አላማዎቹም ኢኮኖሚያዊ ትርፍ ማስገኘት ነው::

ሰ. ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት

እነዚህ ማህበራት ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር መኖራቸውን በደም ምርመራ ያረጋገጡ ዜጎች በመሰባሰብ የሚያቋቁሚቸው ህጋዊ ማህበራት ሲሆኑ እንደማንኛወም ሲቪል ማህበር የሚቆጠሩ ናቸው::

የእነዚህ ማህበራት አላማ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወገኖች እርስ በእርስ በመመካከር፣ በመደጋገፍና በመንከባከብ ከቫይረሱ ጋር በሰላም መኖር ይችሉ ዘንድ የምክር፣ የህክምናና ሌሎች ማህበራዊ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማገዝ በህይወት ተሞክሮአቸውም ሌሎች ለቫረሱ እንዳይጋለጡ ማስተማር ነው::

ረ. የግል ተቋማት

የግል ተቋማት በአብዛኛው አላማቸው ትርፍ የሆነ በጥሬ እቃ አቅርቦት፣ በምርት፣ በስርጭት ወዘተ አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የትምህርት፣ የትራንስፖርት ፣ የቲያትርና መዝናኛ ፣ የመረጃ፣ የሸቀጣሸቀጥ አቅርቦት፣የፋይናንስና ኢንሹራንስ እና መሰል አገልግሎቶችን ለህ/ሰቡ በማቅረብ ትርፍ የሚያገኙ ሆኖም ግን በተ.ቁ ሠ ስር ከተጠ ቀሱት ጋር ሲነፃፀሩ በመጠንና በሰው ሀይል ይዞታቸው አነስተኛ የሆኑትን የሚመለከት ነው::

3. <u>አመለካከት በእነዚህ ተቋማት</u>

እነዚህን ተቋማት በተመለከተ የነበረወን አመለካከት /attitude/belief /ና አመለካከቱን ተከትሎ የመጣውን ተቋማዊ ባህሪይ /Organizational behavior/ በጥሞና ተረድቶ በአንፃሩም ከእውነታውና ከመርህ /Principle/ አንፃር ምን መሆን እንደነበረበት በመመልከት ይህ የህዝብ ንቅናቄ ከእነዚህ ተቋማት የሚጠበቀው አመለካከትና ተቋማዊ ባህሪይ ምንድነው የሚለውን መመለሱ ተገቢ ነው:: የነበረውን አመለካከት ደግሞ ውጪያዊ /ሌሎች ከተቋሙ ውጪ ያሉ አካላት በተቋሙ ላይ/ እና ውስጣዊ /ተቋሙ በራሱና በሌሎች ከተቋሙ ወጪ ባሉ አካላት ላይ/ አመለካከት ብሎ ከፍሎ ማየት የበለጠ አግባብ ነው:: ተቋማቱን አንድ በአንድ እያነሳን እንቃኝ፣ / እዚህ ላይ የምናነሳው አመለካከት አሉታዊውን ሲሆን ይህ አመለካከት ሁሉንም በጥልቅ የሚመለከት እንዳልሆነ ግን ሊሰመርበት ይገባል!/

3 <u>መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች</u>

<u>ሀ. ውጪያዊ አመለካከት</u>

- ብዙዎች እነዚህ አካላትን ለልማት ሳይሆን ለጥቅም የተቋቋሙ ከመንግስት አሰራር፣ አመለካከት፣ አላማ፣.. በተቃራኒው የቆሙ እንጂ የልማት አጋር ያልሆኑ አድርገው ያስባሉ፡፡
- በሌላ በኩል ብዙዎቹ በተለይ በአገራችን ኤች አይቪ/ኤድስ ላይ በንቃት የመሳተፍ በቂ አቅም ያላቸው አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በበቂ መጠን እንዳሉ ያስባሉ፡፡
- በተለይ አለም አቀፍ ደርጅቶች ይዘው የመጡት እውቀትና ልምድ ሁሉ ተገቢ፣ከማህበረሰባችን ነባር እውቀትና ባህላዊ/ማህበረሰባዊ እሴት ሁሉ የተሻለ የማ/ሰቡን ችግር ለመፍታት ብቸኛ መፍትሄ ተደርጎ ይታያል፡፡
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባሉበት ሁሉ ገንዘብ እንዳለ፣ እነዚህ አካላት ለማህ/ሰቡ በሚሰሩት ስራ ላይ  መሳተፍን ጥቅም ከማግኘት ጋር የማቆራኘት አመለካከት በስፋት አለ፡፡ የሚሰሩት ስራም የህብረተሰቡ ሳይሆን የድርጅቶች ጉዳይ ተደርጎ ይታያል፡፡
- እነዚህ አካላት የፈለጉትን ማድረግ የሚችሉ ባሻቸው አቅጣጫ ለመጓዝ እውቀቱም መብቱም የተሰጣቸው ማን ምን ሰራችሁ ፣ "ለምን በዚህ መንገድ አትሰሩም የእኛ ፈላጎት ይሄ ሳይሆን ይህኛው ነው ወዘተ" ብሎ ሊጠይቃቸው የማይቻል አድርጎ የማየት አመለካከት ያስተውላል፡፡
- ሁሉም መያዶች ከመንግስት የተሻለ የልማት አማራጮች፣ ፍፁማንና የህዝብ እውነተኛ አገልጋዮች፣ ከመንግስት ይልቅ  የሚታመኑ፣ በቂ የመፈፀም አቅም ያላቸው፣ አዋጭ /Cost effective/ ናቸወ የሚል አጠ ቃላይ አመለካከት አላቸው፡፡
- "መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /በተለይም ለጋሾች/ እስካሉ መስራት፣ ማረስ፣ ራስን መቻል፣.. ምን ያደርጋል፡፡" የሚሉ ብዙዎቹ ነበሩ፡፡ አሉም፡፡ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ከመታገል ይልቅ ፣ ስለ እርዳታ የማሰብ ዝንባሌ ሰፍኗል፡፡ ኤች አይ ቪን ባለ አቅም ከመከላከልና መቆጣጠር ይልቅ "እኛ አካባቢ አንድም መያድ የለም፡፡" የሚል ስሞታ ይሰማ፡፡ ይህ መያዶችን የችግሮቻችን ሁሉ ብቸኛ መፍትሄ ከማየት አደገኛ አመለካከተ የመነጨ ነው፡፡

ለ. <u>ውስጣዊ አመለካከት</u>

አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከራሳቸውና ከሚያገለግሉት ህ/ሰብ አንፃር የሚስተዋልባቸው የተሳሳተ አመለካከት /በአብዛኛው/፣

- እኛ "ምግባረ ሰናይ" ተቋማት ነን የእለት ደራሽ እርዳታ ከማደል፣ ህክምና ከመስጠት፣ውጪ  ልማት የመንግስት ጉዳይ ነው፡፡
- መንግስት አይታመንም፡፡ ስለዚህ ማኛውም የገንዘብ ድጋፍ በመንግስት ካዝና መግባት የለበትም /በተለይ ለጋሽ ደርጅቶች/
- የእከሌ አገር ተሞክሮ የእገሌ አገር ሳይንስና እውቀት ደቡብ ኦሞ ሀመር ወረዳ ላይ ሙሉ በሙሉ መተግበር አለበት፡፡
- የእኛ ተሞክሮና እውቀት ከህ/ሰቡ ባህላዊና ልማዳዊ እውቀትና ተሞክሮ የተሻለ ነው፡፡ ስለዚህ እውነቱም መፍትሄውም እኔ ያልኩት ነው፡፡

- የጌድኦ ኮቸሬ ወረዳ ህዝብን ችግርና መፍትሄ ከህዝቡ ይልቅ እኔ አዲስ አበባ ላይ ያለሁት ድርጅት አውቃለሁ::
- ህ/ሰቡ ገበሬ ስለሆነ ፣ ያልተማረ ስለሆነ፣ ለዘመናዊ ቴክኖሎጂ የራቀ ስለሆነ ወዘተ እሱን አማክሮ መስራት አያዋጣም በእቅድ በአፈፃፀም፣ በውሳኔ ወዘተ ህብረተሰቡን ማሳተፍ ምን ይጠቅማል::
- "ፈንድ" ይገቬ እስከመጣሁ ለተቀዳሚ የረሀብ ችግሩ "ዳቦ" እስከሰጠሁ እየቀሰፈ ላለው ኤች አይ ቪ/ኤድስ ችግሩ "ወርክሾፐና በራሪ ወረቀት" እስካዘጋጀሁ የዚያ ህ/ሰብ ባህል ፣ ማህበራዊ እሴት ፣ የጎሣ መሪዎች ድምጽ፣ ወዘተ ትኩረት ባይሰጠውም ችግር የለም::
- እኔ በየትም አካባቢ የምፈጽመውን ስራ የሚከታተለኝ /የሚያገባው/ "ፈንዱን" የሰጠኝ አካል ብቻ ነው:: የትኛውም አካል በአዋጅ ይቋቋም ጉዳዩ አይደለም::
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ፣ በውሀ ኩሬ ማጎልበት ፣ ከእኔ የተሻለ ሌላ ማን አለ? ከሌሎች ምንም የምንማረው ነገር የለም::
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስራ ካለ "ፈንድ" ካለ አበል፣ ካለ መኪና፣ ካለ .. እንዴት ይሰራል ህ/ሰቡን ማበረታታት የምንችለው በክፍያ ነው::
- የህ/ሰቡ ብቸኛው አቅም "ፈንድ" ነው
- የመንግሰት ተቋማት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ተሳትፈው ምን ሊፈይዱ ነው የሚል አመለካከት፣
- ህ/ሰቡ አቅሙ ደካማ ስለሆነ፣
- መንግስት ለሚወስዳቸው በጎ ተግባራት እውቅና ያለመስጠት አንዳንዴም የማጥላላት፣
- ሌላው በሁለት ዞኖች ለሚሰራው አቅም ግንባታ /ስልጠና ብቻ በሁሉም ወረዳዎች የHAPCO ቢሮ ተከፍቶ ሳለ /**Establishing woredas and zonal HAPCO offices** '' የሚል ስራ ጨምሮበት/ 16 ሚሊዮን ብር /ያውም በዩ ኤስ ዶላር/ ክልሉ "ፈንድ" እንዲያደርገው ያቀርባል:: የክልሉ HAPCO እስከዛሬ ያንቀሳቀሰው ጠቅላላ በጀት ስንት ነው ?
- ሌላው "ፈንድ" የሚባለውን ነገር አገራችን መጠቀም ስላልቻለች እና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ደግሞ የመጠቀም ብቃቱም ስላለው ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ በየወሩ የልብስ 250 ብር የቤት ክራይ 100 ብር፣ የምግብ 150 ብር፣ ለህክምና 1000 ብር በጠቅላላው በአንድ ወረዳ 150 ሰዎች" የሚል፣ " ስለኮንዶም አጠቃቀም ለወጣቶች ለማስተማር ለ5 ቀን በየቀኑ ብር 70 አበል ለወጣቶች በቀን 500 ብር ለአሰልጣኝ፣ የመኪና ኪራይ፣ ... " የሚል ፕሮፖዛል ያዘጋጃል፣ ድጋፍና እንክብካቤ ማለት ነየወሩ ብር መስጠት፣ የመከላከል ስራ ማለት ፖስተር ማሳተም፣ የግንዛቤ ወርክሾፐ ማዘጋጀት፣ ተጋላጭነትን መቀነስ ደግሞ ለተገኘው ሁሉ በጭፍኑ ሁለት ወይም ሶስት ሺህ ብር መነገጃ መስጠት አቅም ግንባታ ማለት መኪና፣ ሞተር ሳይክል፣ የቢሮ ቁሳቁስ መግዛት ወዘተ እየተደረገ የሚተረጎምበት ሁኔታ አለ::

## ሐ. <u>አስተሳሰቡ የፈጠረው ክፍተት</u>

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ከየአቅጣጫው ያሉ አመለካከቶች እየሰፉ ሄዱና ለልማትም ሆነ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በውጤታማነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንቅፋት የሆኑ ተቋማትና ግለሰባዊ/ማህበራዊ ባህሪያት ፈጠሩ::

- መንግስትና ህ/ሰቡ በእነዚህ አካላት የሚሰሩ ስራዎች ሁሉ ከፍተኛ የገንዘብ ምንጭ ስላላቸው በስራዎቹ ሁሉ መሳተፈም ሆነ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ አይደለም የሚል እምነት አዳበረ በእነዚህ አካላት የልማት ስራዎቹ ለመሳተፍም ክፍያ መንግስትንና ህ/ሰቡን ለማገዝ በሚሰሯቸው ቅድመ ግዴታ ሆነ:: ዘርፈ ብዙ የኤድስ ምላሽ /Multisectoral Response/ እዚህ ላይ ውህ በላው::
- በጎ ፈቀደኝነት ተረሳ ፣ የጥንቱ የመደጋገፍ፣ የመረባረብ ባህል፣ የመተዛዘን ስሜት ተሸርሽሮ አለቀ
- ህ/ሰቡ በብብቱ ያለውን ትልቅ አቅም ረስቶ ቆጥ ላይ ባለው የውጪ ድጋፍ ተመካ:: የጠባቂነት ባህሪው ከግለሰብ አልፎ ወደ ማህ/ሰብና ተቋም ደረጃ አደገ:: ተረጂነት የማያሳፍር ተገቢ ጉዳይ ሆነ::

- በምግብ ለስራ ዛሬ የሰራውን እርከን ለነገ ሌላ ምግብ ለስራ ማታ ላይ ማፍረስ፣ በቀን የተከለውን ችግኝ በምሽት መንቀል ፣ማገዶ ቆጣቢ ምድጃን እንደልምድ የማስተዋወቂያ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ከተረዳ በኋላ አበልና ምድጃ ሊሰጠው አበሏን ወደ ኪሱ ከቶ ምድጃውን ሰብሮ ወደ ቤቱ መግባት በረከተ:: ወጣቱ ስለ ራሱ ጤንነት ለመማር ለራሱ የሚሆን ማዕከል ለመስራት፣ የራሱን ክህሎትና ፈጠራ ለማዳበር ፣ እድሉ ሲሰጠው ካልተከፈለኝ /ያለ አበል/ አልፈልግም “ ማለትን እያመጣ ነው::
- ይህ 70 ብር አበል አገኘ ስለራሱ ጤንነት የተማረ ወጣት ደግሞ ነገ ሌላው መጥቶ ”በበጎ ፈቃደኝነት የቤት ለቤት እንክብካቤ” እንዲያደርግ ሲጠይቀው የሚሰጠው መልስ የታወቀ ይሆናል::
- መንግስት በቀላል የህዝብ ተሳትፎ እየሰራቸው የነበሩ የልማት ስራዎች እንቅፋት ገጠማቸው:: ካለ አበል ለመስራት ፈቃደኝነቱ እየቀጨጨ ሄደ:: እንግዲህ በዚህ መልኩ ከላይ የተዘረዘሩት የአመለካከት ችግሮች እየተወሳሰቡ እነዚህንና መሰል ችግሮች እያመጡ ነው::

- መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም ራሳቸው ንጉስ የመሆን አይነት ተቋማዊ ባህሪይ ፈጠሩ:: ሁሉ ፕሮግራማቸውን በራሳቸው አቅጣጫ ፣ አሰራራቸውን ለእነርሱ እንደተመቸ ተቆጣጣሪ የሌላቸው የማህ/ሰቡን አቅም እያሳደጉ ራሱን ከአደጋ እንዲጠብቅ ከማስቻል እንዲሁም ችገሩን ከምንጩ አድርቆ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከችግር ነፃ ከማድረግ ይልቅ ላይ ላዩን በመነካካት፣ የእለት ደራሽ እርዳታ በመስጠት፣ በወርክሾፕና በፖስተር ወዘተ ስራ ብቻ ላይ በማተኮር እድሜን ማራዘም ፣ የገቢ ምንጭን ማጎልበት ትክክለኛ አቅጣጫ ሆነ::
- “ፈንድ” አለ ሲባል ብቻ ከዚህ በፊት የተሰራን ፕሮፖዛል ፊደል በመቀየር አልያም የታወቀ “Consultant” አሳምሮ እንዲጽፈው በማድረግ ሂደው ያላዩትን የችግር መዓት በመዘርዘር፣ መሸከም ከሚችሉት አቅም 10 እጥፍ የሚበልጥ በጀት መጠየቅ ልማድ ሆነ:: አንዳንዱ በሶስት ቀበሌው ውስጥ ለሚሰራው ስራ 1 ሚሊዮን ብር ፣ መኪና ፣ ሞተር ሳይክል፣ የስምንት ባለሙያዎች ደመወዝ ጨምሮ ይጠይቃል:: ይህ ደግሞ የሚሰሩ ስራዎች ሁሉ ውጤታማነታቸው ሳይሆን የሚያስገኙት “ፈንድ” መጠን ላ ብቻ እንዲያተኩር አድርጓል:: እነዚህ ያለ ጥንቃቄ የሚዘጋጁ የስራ እቅዶች

ተገቢውን አቅጣጫ እስኪይዙ ድረስ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ፈጀ:: የተገኘውን ድጋፍ የመጠቀም ፍጥነታችን የባሰ ቀርፋፋ ሆነ::

- ራስን ከማንም በላይ የመገመቱ፣ የህ/ሰቡንና የሌላውን እውቀት ፣ ተሞክሮ የመዘንጋቱ ሁኔታም፣ የጋራ መማማርን፣ የተሻለ አቅም መፍጠሩን፣ እርስ በእርስ ተደጋግፎ ለበለጠ ውጤት መስራትንና የመሳሰሉ ጠቃሚ ባህሎችን አመከነ:: የማ/ሰቡም አቅምና የራሱን ችግር በራሱ የመፍታት ብቃት ከነበረበት ፈቀቅ ሳይል በረካታ ጊዜና ገንዘብ ባከነ::
- በአጠቃላይ ህ/ሰቡ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሚሰሩ የትኛዎቹም ስራዎች ዙሪያ ያለው አመለካከት ተበላሸ ፣ ንቁ ተሳፎውም በእጅጉ ቀነሰ:: ይህ ደግሞ የመከላከልና መቆጣጠር ስራው በተፈለገው ፍጥነት እንዳይሄድ አደረገ::

## *መ. ልንቀበለው የሚገባን እውነት*

- መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ክፍተት የሚሸፍኑ፣ በእለት ደራሽ ስራ ላይ ብቻ መሰማራት ያለባቸው፣ በራሳቸው ስትራተጂ፣ ማስተር ፕላን፣ አቅጣጫ፣.. የሚንዙና ፣ እምነታቸውን፣ አመለካከታቸውን የሚፈልጉትን አይነት አሰራር፣ ወዘተ በህ/ሰቡ ላይ የሚጭኑ አካላት ሳይሆኑ የመንግስትም ሆነ የህ/ሰቡ የልማት አጋሮች፣ ከመንግስትና ከህ/ሰቡ ጋር በመምከር በሚያወጡት የጋራ ስትራተጂ፣ ማስተር ፕላንና አቅጣጫ እርስ በእርስ በመደጋገፍ አብረው የሚሰሩ ተጠሪነታቸው ለማንም ሳይሆን ለሚያገለግሉት ማህ/ሰብ የሚያገለግሉትን ማህበረሰብ በጎ እሴቶች የሚያዳብሩ አቅሙን እየገነቡ ራሱን እንዲችል ዘላቂ ልማት እንዲያመጣ የሚያደርጉ አካላት ሊሆኑ ይገባል:: መንግስትም ሆነ ህ/ሰቡ ይህንን አመለካከት መቀበል፣ አብሮ የማቀድ ስራዎችን የመገምገምና የመማማርን ባህል ማዳበር ተገቢ ነው:: ወቅቱም ይህንን ይሻል::ብዙዎቹም እየተረዱት ነው:: ግልጸኝነት ማህበረሰባቀፋዊነት፣ ተአማኒነት፣ አሳታፊ የሆነ አሰራር የዘርፈ- ብዙው የኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስርዓቱ ዋነኛ መርሆዎች ሆነዋል:: ስርዓት አንድ አካል መሆን ወዘተ አሁን እጅግ ወሳኝ እየሆነ መጥቷል::

- በሌላ በኩል ምንም ያህል "ፈንድ" ቢኖር ብቻውን ችግራችንን አይፈታም:: ችግራችንን ለዘለቄታው የሚፈታው እውነተኛ አዎንታዊ ስር ነቀል የሆነ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ተቋማዊ የባህሪይ ለውጥ ስናመጣ ይህ ደግሞ "በፈንድ" ብዛት ሳይሆን የችግሩ ተጠቂ የሆነውን ህ/ሰብ የመፈትሄው ባለቤት ሆኖ በራሱ ተሳትፎ የራሱ ችግር የሚፈታበት አቅም የሚመጣ ነው:: ይህ የሚያስፈልገው ከገንዘብ ይልቅ ቁርጠኝነትን ነው:: እውነታውን አምኖ መቀበልን ነው::

- እስከዛሬ ለአገራችን ከተሰጠው የውጭ ልገሳ በሺህ እጥፍ የሚልቅ አቅምና ሀብት ህ/ሰቡ ውስጥ አለ:: ዘላቂ ላልሆነ የእርዳታ ገንዘብ ብለን ዘላቂ የሆነውን እምቅ የህ/ሰብ አቅምን ሀብት ማምከን ወንጀልና ያለማወቅ አልያም ራስን ወዳድነት ነው:: ብዙ የተወራለት የአለም ባንክ የ3 ዓመት ብድር መጠን እያንዳንዱ የኢትዮጲያ ህዝብ በየወሩ 30 ሳንቲም ቢያዋጣ በ3 ዓመት የሚያጠራቅመው ነው:: ከዚያ ብዙ እጥፍ የሚልቅ አቅምና እምቅ ጉልበት ግን ማ/ሰባችን ጋ አለ:: ያንን መጠቀም ማህ/ሰብን መሰረት ያደረገ ስራ መስራት እንጂ እንደእስካሁኑ አካሄድ ኤች አይ ቪ/ኤድስን መቼም አናቆመውም:: መፈትሄው መጀመሪያ ባለን መጣር ጠባቂነትን ማስወገድ የህ/ሰቡን አቅም አምኖ መቀበል::

- ሌላው ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነፃር የእኛ አገር መንግስታዊ ያልሆኑ አገር በቀል ድርጅቶች ገና በመዳህ ላይ ያሉ ናቸው:: በቂ አቅም የላቸውም ገና እያቆጠቆጡ ፣ገና እየተንገዳገዱ ናቸው:: አቅማቸው ሊገነባ ፣ ከዚህ አንፃር ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል:: ተገቢው የአቅም ግንባታ ሊደረግ የሚችለው ደግሞ ይህንን ሀቅ መያዶቹም ሆኑ ሌሎች አካላት አምነው ሲቀበሉ ነው:: ካለበለዚያ በተሳሳተ ግምት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንጓዛለን::

- ላይ ላዩን በማረስ አስፋልት አስፋልቱን በመጓዝ ከተማ ከተማውን በማጨናነቅ በራሪ ወረቀት ፣ ፖስተር፣ የግንዛቤ ማዳበሪያ የአዳራሽ ውስጥ ጉባዔ በማካሄድ እየሰበሰቡ አበል በመስጠት፣ በአማካሪ ከላይ አሰርቶ ህ/ሰቡን ያውልህ በማለት ወዘተ የትም አይደረስም:: ታች ወርደን ከህብረተሰቡ ጋር የችግሩን ስር ቆፍረን፣ ምንጩን አግኝተን ሀላፊነቱንም ለህ/ሰቡ ለራሱ ሰጥተነው ራሱ ምንጩን እንዲቆጣጠር በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ችግሮቹንም በዚሁ ዘዴ እንዲፈታ ስናደርግ ዘላቂ መፍትሄ ይገኛል:: ራስ ምታቱን ሳይሆን የራስ ምታት ምንጭ /መንስኤ/ ማከም መቻል አለብን:: ትኳንን ለማጥፋትም ቤቱን ማቃጠል ተገቢው መፍትሄ አይደለም:: ለአንድ የራበው ሰው ለጊዜው አሳ አጥምዶና ጠብሶ መስጠቱ መፍትሄ ይሆን ይሆናል ፣ ዘላቂው መፍትሄ ግን እንዴት እንደሚጠመድና እንደሚጠበስ ማስተማሩ ፣ ማጥመጃውንና መጥበሻውን መስጠቱ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

- መያደም ሆነ ሌላው የማ/ሰብ አጋር አካል፣ እስከመቼ እርዳታ እየሰጠ ሊኖር ነው:: ህ/ሰቡ ሁሌም ከተረጂነት ካልወጣ ችግሩ በራሱ መፍታት ካልቻለ የድርጅቱ መኖር የፈየደው ምን ሊሆን ነው? የመያድ ድርሻስ ህ/ሰቡ የሚሰራውን ስራ ተክቶ መስራት ነው? ወይስ ህ/ሰቡ መስራት ከሚችለው ሌላ የተሻለ የመስራት ብቃት እንዲኖረው ማስቻል? አሰራሩን ማሻሻል፣ የተቀላጠፈ ማድረግ ከአቅሙ በላይ በሆነው ዘርፍ ተሳትፎ ማገዝ ወዘተ መሆን ነበረበት የመያድ አካላት ድርሻ አላማችንም ይህ ሊሆን ይገባል!

- እውነተኛ ወጤት ተኮር የሚመጣው ሁላችንም በተራቀቅንበት፣ በተሻልንበት ዘርፍ ስንሰራና የአንዳችን ስራ በሌላኛው ስራ ሲደገፍና ሲሟላ ብቻ ነው:: የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋት ከጤና ቢሮ የተሻለ ፣ በትቤቶች ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሜይስትሪም ለማድረግ ከትምህርት መዋቅር የተሻለ ምን አለ? አቅም የለም አመቺ ስርዓት የለም ብንል አንኳን ውጤታማው አማራጭ ይሄ መዋቅር እስከሆነ ድረስ ስርዓቱን/አቅሙን እንዴት እንገንባው ? ብሎ ነው መጠየቅ:: በአጠቃላይ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሁሉም ዘርፍ ለመግባት ያለ አቅማችን የማንወጣውን ሸክም በራሳችን ከምንጭን በአቅማችን ልክ የእኛ /Comparative advantage / የሆነውን ስራ መርጠን በጥራት፣በውጤት እየሰራን አቅማችንን ማሳደጉ ህ/ሰባችንንም መጥቀሙ ልንከተለው የሚገባን አቅጣጫ ነው::

- በተለይ የህ/ሰቡን የፈፃሚ አካላትን፣ ወዘተ አቅም በመገንባት ፣ ራሱን በማስቻል፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የእለት ተእለት ስራው አካል እንዲያደርግ በመደገፍ፣ ያለንን የቴክኒክና የሙያ ክህሎት ለእነዚህ ዘላቂ ተግባራት ማዋሉ እወነተኛው አካሄድ ነው::

- አቅም ከየትም አይመጣም ከተግባራዊ ተሳትፎና ስራ እንጂ የህ/ሰቡን አቅም መፍጠር ካለብን በሁሉም የስራ ሂደት ማሳተፍ ይጠበቀብናል፡፡ አቅም የለውም በሚል የእራሱ ስራ እንጂ ልንሰራለት አይገባም፡፡ መኪናውን ሌላው እየነዳለት ሾፌር የሆነ የለምና መሪውን ይጨብጥ ራሱ ይንዳ!

3.2 **ሲቪል ማህበራት /Civil Society Organization/**
<u>ውጫዊ አመለካከት</u>

- በተለይ በደርግ ስርዓት ከነበረው የአኢወማ፣ አኢሴማ፣ ወዘተ ተሞክሮ በአብዛኛው የህ/ሰብ ክፍል በውስጡ የፈጠረው አመለካከት ሲቪል ማህበራት ከፖለቲካ ተቋማትና ወገንተኝነት ጋር አቆራኝቶ የማየት ሁኔታን ነው፡፡
- አብዛኛዎቹ /በተለይ የሴቶች፣ የመምህራን፣ ወዘተ/ ማህበራት በከፊል የሚደጎሙት ከመንግስት በጀት መሆኑ ደግሞ አሁንም በእነዚህ ማህበራት ዙሪያ የነበረው አመለካከት የበለጠ ሊያጠነክረው ይችላል፡፡

- አንዳንድ በራሳቸው ጊዜ የተቋቋሙ የሙያ ማህበራት ደግሞ በአብዛኛው ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸው ቁርኝት ወይ በህብረተሰበ ወይ በፖለቲካ አመራሩ ዘንድ ስለማህበራቱ የተዛባ አመለካከት እንዲፈጠር ሲያደርግ የነበረበት ሁኔታም ነበር፡፡

- በአጠቃላይ እነዚህ ማህበራት የልማት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ/አጋሮቻችን ይሆናሉ የሚለው አስተሳሰብ በአብዛኛው ዘንድ የለም፡፡ እንደውም የሴቶች ማህበር ተነስቶ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለቡና ቤት አስተናጋጆች የአቻ መምህራን ስልጠና ቢሰጥ ወይም እንዲሰጥ ድጋፍ ቢደረግለት የፖለቲካ ድጋፍ ስላለው እንጂ አሁንም ምን አግብቶች ነው፣ ምን አቅም አለው ይባላል፡፡ ማህበራትን እንደዋነኛ አጋር ተቀብሎ አብሮ ለመስራት የሚያስችል አመለካከት አልተፈጠረም፡፡

- አመራሩ የሲቪል ማህበራትን በኤች አይ ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ የማበረታታት ሁኔታ አናሳ ነው፡፡ አንዳንድ የፖለቲካው ቡድኖችም የእነዚህን መሰል ማህበራት በልማት መሳተፍ፣ ከፖለቲካ ጋር የሚያያይዙበት ጊዜ አለ፡፡

<u>ለ. ውስጣዊ አመለካከት</u>

- እነዚህም ቀደም የነበረው የተልዕኮ ውዥንብርና የፖለቲካ ወገንተኝነት የፈጠ ረው የአመለካከት ችግር በማህበራቱ አባላትና የውስጥ አመራር ላይም ተመሳሳይ ስሜት ይኖረዋል።
- ማህበራቱ በትክክል ኤች አይ ቪ/ኤድስ የእኛ ጉዳይ ነው ብሎ የመቀበል ችግር አለባቸው።
- የማህበራቱ አመራር አሁንም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ሞልቶታል የሚለው አስተሳሰብ ተጋሪ መሆናቸው አይቀርም።
- በመሆኑን በሠራተኛው ማህበር ውሰጥ ያለው አመለካከት የኤድሰ ችግር የሴክሪታሪያት፣ የመያድ፣የጤና ቢሮ እንጂ የእሱ ችግር ሰራተኛው ደመወዝ ሲቆረጥበት መከራከር ፣ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ ሲረቅ ሰራተኛውን ወክሎ መደራደር፣ ወዘተ ብቻ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ይኖራል። በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ ለኤድስ ህሙማን ሰራተኞች የነፃ መድህኒት አገልግሎት፣ ለቫይረሱ ከሚያጋልጡት መብቶች የመጠበቅ፣ መብቱ እንዲከበርለት የሚል ሃሳብ ማንሰቱ የሌላው ጉዳይ ነው።

## ሐ. <u>አመለካከቱ የፈጠራቸው ክፍተቶች</u>

- እንደነዚህ ያሉት አመለካከቶች በአጠቃላይ የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ በኤች አይ ቪ/ኤዝድሰ ዙሪያ በጣም አናሳ እንዲሆን አድርገዋል።
- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ቀሰ በቀስ የየማህበራቱን አባላት እያመናመነ የማህበራቱን ህልውናም ከአደጋ ሊጥል እንደሚችል እንዳይረዱ አመለካከቱ ጋርዶባቸዋል።
- የተለያዩ ወገኖችም ከእነዚህ አካላተ ጋረ አብረው የመስራት አመኔታን እንዲያጡ በህ/ሰቡ ዘንድም ተሰሚነትና ተቀባይነት እንዲያጡ በር ከፍቷል ወይም ይከፍታል።
- መንግሰትና በኤቸ አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱት ሀይሎች ሰፊ መሰረትና ከፍተኛውን ህዝብ ሊደርስ የሚችለውን ውጤታማ አጋር እስከዛሬ ከጎኑ ሳይሰለፍ እንዲቀር አድርጓል።

## መ. <u>ልንቀበለው የሚገባን እውነት</u>

- ሲቪል ማህበራት የተለያዩ የህ/ሰብ ክፍሎችን በቀላሉ ለመድረስ የሚያስችሉ፣ በተለይም በኤች አይ ቪ/ኤድሰ መከላከልና መቆጣጠር ትግሉ ወሳኝ የሆኑ አጋሮች ናቸው።
- ሲቪል ማህበራቱ በሚኖሩበት ህ/ሰብም ሆነ በሚወክሉት አባል የጤና፣የሰብዓዊ መብት፣ የፍትህ፣ ወዘተ ጉዳዮች ተሳትፈው ጠቃሚ ለውጥ የማምጣት ሃላፊነት እንዳለባቸው መረዳት ተገቢ ነው።
- መምህራን፣ ወዛደር፣ገበሬው ፣ ሴቶች፣ .. በኤች አይ ቪ/ኤድስ እየተጠቁ ባሉበት ሁኔታ ከመምህራን፣ ሠራተኞች ፣ የሴቶች፣ የአምራቾች የህብረት ስራ ወዘተ ማህበራት ቀድሞ በኤድስ ዙሪያ መሰለፍ ያለበት ሌላ ሊኖር አይገባም የሞራል ጥያቄም ያስከትላል።
- እነዚህ ማህበራት ቢነቁና ቆጭ ብለው ቢያስቡ ጉዳዩ የእኛ ጉዳይ ነወ ብለው በጣም በቀላል ወጪና ቀልጣፋ በሆነ አሰራር በርካታ ዜጎች / የማህበራቱን አባላተ/ ነፃ የART ህክምና ማግኘት በቻሉ ነበር። በአሁኑ ሰዓት በማህበራቱ አባላት ላይ እየደረሰ ያለውን የኤድስ ሞት ባልደረሰ ነበር።

- በእርግጥ በመከላከሉ ረገድ በተለይ የክልሉ መምህራን፣ ወጣቶችና ሴቶች ማህበራት ተነሳሽነት አሳይተዋል፡፡ ሆኖም ግን በጣም ብዙ ይቀራል፡፡ ከማህበራቱ ከሚጠበቀው እልህ አስጨራሽ ስራና የሞራል ሃላፊነት ጋር ሲነፃፀር ምንም አልሰሩም፡፡

- የስራ ቦታ የ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲና መምሪያ እንዲወጣ፣ በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ ፣ የፋብሪካ ሰራተኞች ፣ የህብረት ስራ ማህበር አባላት፣ ወዘተ የART Fund እንዲቋቋም ፣ ወዘተ ቅስቀሳና ግፊት በማድረግ የራሳቸውንም ደጋፍ በመስጠት እነዚህ ማህበራት ከየአቅጣጫው ቢሳተፉ ኖሮ በጣም በጊዜ እውን ሆኖ በርካታ ዜጎች ከህመም ስቃይና ሞት ተርፈው፣ ቤተሰቦቻቸውና ስራቸው ከቀውስ ወጥቶ ማየት ቢቻል ነበር፡፡

- ሌላው ወሳኝ እውነት ኤች አይ ቪ/ኤድስ የትኛውም የፖለቲካ አካል የቆመለትን ህዝብ ከአደጋ የከተተ እስከሆነ ህዝቡን ከዚህ አደጋ በማውጣት ዙሪያ የሚለያይ የፖለቲካ ርዕዮት አይኖርም፡፡ ስለዚህ የትኛውም የፖለቲካ አቋም፣ ወገንተኝነት ይኑረው ህ/ሰቡን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ አደጋ ለማዳን ወሳኝ አማራጭ የሆነ ሁሉ በስራው መሳተፍ እጅግ ጠቃሚ ተደርጎ መውሰድ አለበት፡፡ መደገፍም አለበት፡፡ አግባብ የማይሆነው ለዚህ ህዝብን የማዳን ተግባር የተሰጠውን ሃላፊነትና ድጋፍ ለፖለቲካ ጥቅም ያዋለው እንደሆን ብቻ ነው፡፡
- አሁንም፣ ወደፊትም የእነዚህ ማህበራት ተሳትፎ የማይተካ በጣም ጠቃሚ ሚና የሚኖረው ነው፡፡
- ይህንን የሲቪል ማህበራቱን ሚና በሚገባ አጢኖ ዘላቂ የሆነ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከሁሉም ወገን ይጠበቃል እነዚህ ማህበራት ወደዚህ መስመር ገብተው የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጡ ሰፊ የአቅም ግንባታና የአድቮኬሲ ስራ የሚሻ የመሆኑን እውነትም መረዳት ተገቢ ነው፡፡

### 3.3 የብሄረሰብ ልማት ማህበራት

<u>ሀ. ውጫዊ አመለካከት</u>

- በአብዛኛው በእነዚህ ማህበራት ዙሪያ ከውጫዊ አካላት ምናልባትም ከመንግስት አካላት ውጪ/ ያለው አመለካከት ከሞላ ጎደል ከሲቪል ማህበራት ዙሪያ ካየናቸው ጋር ይመሳሰላል፡፡
- ምንም እንኳን እነዚህ ማህበራት በአወቃቀርና በአደረጃጀት ከአገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ጋር ልዩነት ባይኖራቸውም፣ ማህበራቱ በመንግስት የሚደገፉ በመሆናቸው ብቻ ብዙዎች ከመንግስት መ/ቤቶች ጋር በእኩል አይን ያዩዋቸዋል፡፡ ለጋሽ አካላትም በእነዚህ ማህበራት ላይ አመኔታ ያለመኖር ስሜት አላቸው፡፡

<u>ለ. ውስጣዊ አመለካከት</u>

- በክልሉ ብዙ የልማት ስራዎችን እየሰሩ ያሉ በርካታ የብሄረሰብ የልማት ማህበራት ቢኖሩትም ወደ ኤድስ ምላሽ ለመግባት ዘግይተዋል፡፡ ምናልባትም

ሰባቱ ከሚሆኑ የክልሉ የልማት ማህበራት በስተቀር ሌሎቹ ወደዚህ አንገብጋቢ ጉዳይ ስለመግባታቸው መረጃ የለንም::

- ለዚህ ምክንያቱ በከፊል ሌላውን የልማት ስራ ከኤድስ የማስቀደምና ለኤድስ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆን ነው::
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሌሎች ስራ አድርጎ የማሰብ ሁኔታም ይኖራል::
- ራስን እንደሌሎች መያዶች ቆጥሮ ለጋሽ አካላትን ድጋፍ መጠየቁን እንደአግባብ ያለማየትም ሊሆን ይችላል::

## ሐ. <u>አስተሳሰቡ የፈጠረው ክፍተት</u>

- ተቋማቱ በኤች አይ ቪ/ኤድሰ ዙሪያ በስፋት እንዳይሳተፉ መሰናክል ሆኗል::
- በተቋማቱ የማስፈፀም አቅም በሚፈለገው መጠንና ፈጥነት /ከአገር በቀል መያዶች ጋር ሲነፃፀር/ እንዳያድግና ራሳቸውን ችለው ሰፊ መሰረት ያለው ስራ እንዳይሰሩ ምክንያት ሆኗል::
- ከተለያዩ ለጋሽ አካላት፣ ኤቸ አይ ቪ/ኤድስን ከሚያስተባብሩ ሀይሎችና በዚህ ዙሪያ ከተሰማሩ አጋሮቸ ጋር የቀረ ግንኙነት፣ የልምድ ልወውጥና መደጋገፍ እንዳይኖር አድርጓል::
- እዚህ ላይ ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነዚህ ተቋማት ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር እያሳዩ ያሉት ቅርበትና ለጋሾችና ሌሎች ለጋሽ ድርጅቶችም የልማት ማህበራቱን እንደጠቃሚ አጋሮች የመቁጠር አካሄድ መልካም አጋጣሚና ተስፋ እየፈጠረ ነው::
- በተለይ ኋላ ቀር የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሽፋን በሌላቸው የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ በማህበራቱ አማካኝነት የተፈለገውን ስራ ለመሰራት የመቻሉን አጋጣሚ እንዳንጠቀምበት መንስኤ ሆኗል::

## መ. <u>ልንቀበለው የሚገባን እውነት</u>

- የህ/ሰቡን ቋንቋ ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ጠብቀው ታችኛው የህ/ሰብ ክፍል ድረስ ዘልቀው ፣ ህ/ሰቡን ያሳተፈ ውጤታማ ስራ በመስራት ከእነዚህ የልማት ማህበራት የተሻለ አማራጭ የለም::
- በየደረጃው የሚገኙ የፖለቲካና የአስፈፃሚ ተቋማት አመራሮች፣ የእምነትና የጎሣ መሪዎች ወዘተ በቀላሉ በማሳመን በኤድስ ዙሪያ የሚፈለገውን ዘርፈ ብዙ ምላሽ በፍጥነት እንዲሰፋፋ የብሄረሰብ የልማት ማህበራት ተሳትፎ ወሳኝ ነው::
- በእርግጥ በአንዳንድ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ያሉ ማህበራት የአቅም ውሰንነት አለባቸው :: ሆኖም ግን እንደ ወላይታ፣ ጉራጌ፣ ጎጎታ ኬር፣ከፋና ጌዲኦ ልማት ማህበራት ያሉት በክልላችን ከሚገኙ በርካታ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብዙ እጥፍ የተሻለ ጠንካራ ስራ የመሰራት ብቃት እንዳላቸው በተግባር አሳይተዋል::
- በተለይ በመያዶች ያልተደረሱባቸውን ዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌዎች በሚገባ ለመሸፈን ወሳኝ አማራጮች እነዚህ ማህበራት መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል::
- ከፋ ዞን ውስጥ አንድም መያድ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለመስራት ጥያቄ ባላቀረበበት ሁኔታ የመጀመሪያውን ጥያቄ አቅርቦት አምስት ወረዳዎችን

መሸፈን የቻለው ከፋ ልማት ማህበር ነበር፡፡ በወላይታና ጉራጌም በመያድ ያልተያዙ ወረዳዎችን ለመሸፈን ያስቻሉን የየዞኑ ልማት ማህበራት ሲሆኑ በተለይ የጉራጌ ዞን ልማት ማህበር ከፕሮጀክት ወጪው ግማሽ ያህሉ በህ/ሰቡና በወረዳ መስተዳደር እንዲሸፈን ማድረግ ችሏል፡፡ይህንን አይነት ሁኔታ ለመፍጠር የቻለ አንድም ፈፃሚ አካል መኖሩ መረጃ የለንም፡፡

- ከተጠያቂነት አንፃር ብናይም ከሌሎቹ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የተሻለ አንፃራዊ ተጠያቂነት እንዳላቸውና ማህበራቱ ያላቸው የፖለቲካውም ሆነ የአመራሩ ጠንካራ ድጋፍ ስራዎችን በሚፈለጉት መጠንና ሁኔታ በተሻለ ፍጥነትና ውጤታማነት እንዲሁም በቀላል ወጪ ለመፈፀም መቻላቸው ሌላው ጠቃሚ ጎን መሆኑ ሊሰመረበት ይገባል፡፡
- ከላይ የተዘረዘሩት እውነቶች በክልሉ የፀረ-ኤች አይ ቪ/ኤድስ የህዘብ ንቅናቄ ውስጥ የብሄረሰብ የልማት ማህበራት የጎላ ሚና እንደሚኖራቸው ያሳዩናል፡፡

መ. ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት /CBOs/

<u>ውጪያዊ አመለካከት</u>

- ብዙዎቹ አካላት እነዚህን በየቀዬው ያሉ ተቋማት ከተለመደ ባህላዊው አገልግሎቶቻቸው ውጪ ሌላ ሚና እንዳላቸው ያለማወቅ
- ቢያንስ የእነዚህ ተቋማት ባሉበት ሁኔተ መኖርና መቀጠል በራሰ በማህበረሰብ የእለት ተእለት ህይወትና ልማት ላይ ለሚኖረው አዎንታዊ ሚና ተገቢውን እውቅና ያለመሰጠት፣
- የተቋማቱ አባላት የሚያዋጡት አሰር ሳንቲም ሆነ የሚያፈልቁት ሀሳብ ለልማቱ ፋይዳ እንደሌለው፣
- ኋላ ቀር ፣ ከጊዜው ጋር የማይራመዱ፣ እንደውም ለልማት እንቅፋት እንደሆኑ አሁን ላሉት ችግሮች መፈጠር መንስኤ አድርጎ የማየት፣
- በአንዳንዶቹ ዘንድ ደግሞ ከእነዚህ የማ/ሰብ ተቋማት ጋር አብሮ ለመሰራት የሚያችል አደረጃጀት፣አሰራርና የቴክኒክ አቅም ስለሌላቸው በአጋርነት ለመቀበል የማቻል
- ለምዝበራ፣ ወገንተኝነት ፣ ወግ አጥባቂነት፣ ኢ -ፍተሀዊነት ወዘተ የተገለጡ፣ የሴቶችን፣ ህፃናትን .. መብቶች ለመርገጥ ምክንያት የሆኑ
- በተለይ የወጣት ክበባትን የባሰ የወጣቱን ስነ ምግባር የሚያበላሹ አላስፈለጊ ቡድኖች አድርጎ የመቁጠር ፣ ሁኔታዎች በተለይ በወላጆች ዘንድ ይሰተዋላል፡፡ የልጆቸን ሀሳብ ደምጹና ፍላጎት ለመስማት ያለመፈለግም አለ፡፡ ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም የልጅ ነገረ ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ ወዘተ በሚሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች

<u>ውስጣዊ አመለካከት</u>

- በኤች አይ ቪ/ኤድስ ፣ በልማት፣ በሴቶች እኩልነት፣ ወዘተ መካከል ቁርጠኝነት መኖሩን ያለመገንዘብ

- ተቋማቱ አሁን ካላቸው የተለምዶ አሰራር ውጪ ሌላ ሊሰሩ እንደማይችሉ፣ አሁን የያዙት አካሄድም ፍፁምና አንዳችም እንከን የሌለው እንደሆነ የማሰብ
- በተቋማቱ ውስጥ የአመለካከት፣ የአሰራር፣ የአደረጃጀትና የስትራተጂክ አቅጣጫ ለውጥ ለማምጣት መሞከር እንደማይታሰብ፣ እንደውም አደገኛና ባህልን ፣ እምነትን የሚፃረር አድርጎ የማየት፣
- ዘመናዊ የሚባለው አቅጣጫ እንደውም ለተቋማት ህልውና አስጊ እንደሆነ ፣ አልያም ወደ ዘመናዊ ዘቅጣጫ ለመጓዝ ከተቋማቱ አቅም በላይና የማይቻል ጉዳይ መሆኑን የመቀበል ሁኔታ አለ። ለዚህም የሚያመች መንገድም እንደሌለ የመደመደም፣
- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከተቋማቱ ህልውና ጋር ግልፅ ቁርጠኝነት የለም ከሚል መደምደሚያ የመድረስ፣
- አንዳድ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ልማት አጋርነት የተሸጋገሩ የማ/ሰብ ተቋማትም ራሳቸውን እንደ አንድ መንግሰታዊ ያልሆነ ድርጅት /NOs/ የመቁጠር ፣ ለስራቸው መቀጠልም ከሚወክሉት ማ/ስብ
- የወጣት ክበባት ከሙዚቃ፣ ድራማና ኳስ ጨዋታ ውጪ ሌላ አላማና ሚና እንደሌላቸው የሚያምኑ በረካታ ክበባት አሉ።

## አስተሳሰቡ የፈጠረው ክፍተት

- በተለይ " ሰለጠንኩ " የሚለውና ዘመናዊ ነኝ ባዩ የህ/ሰብ አካል ከእነዚህ ተቋማት ርቆ በራሱ ፍልስፍናና የተናጠል ስራ እየተጓዘ ይገኛል።
- በተለያዩ የልማት ስራዎች /ኤች አይ ቪ/ኤድስን ጨምሮ የተማሩ ሀይሎች፣ መንግስትና ሌሎች ለጋሽ አካላት አነዚህን ተቋማት ዘለው በቀጥታ ወደ ህ/ሰቡ ለመድረሰ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ውጤቱ የተጠበቀውን ያህል አልሆነም።
- እነዚህ ተቋማትም በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመዋጋት እንቅሰቃሴ ውስጥ ከመሳተፍ ይልቅ በተለመደው ተግባራቸው /ሲሞቱ መቅበር፣ ንፍሮና እዝን መውሰድ፣ ባልና ሚሰት ማሰታረቅ፣ በድንበር ግልግል ወዘተ የመሸምገል፣.. አይነት ስራዎቸን የመቀጠል፣ አሰራርን ፣ አደረጃጀትን ፣ ሰትራተጂክና ከጊዜው የልማትና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጥያቄዎች ጋር ለማስታረቅ እንደይሞክሩ ዳርጓቸዋል።

- በተለይ ወጣት ክበባት፣ እድሮችና የመሳሰሉት ተቋማት የራሳቸው ራዕይ ኖሯቸው ባላቸው ተሰሚነትና አግባብነት ለኤች አይ ቪ/ኤድስ አጋላጭ የሆኑ ማህበራዊ ተግባራት በመቅረፉ ስራ እንዳይሰማሩ እንቅፋት ፈጥሯል።
- ህብረተሰቡ ከነዚህ ተቋማት በሚያገኘው መረጃና በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሌሎች አካላት በሚሰራጨው መረጃ ያለመጣጣም የተነሳ ለከፍተኛ ውዥንብር ተጋልጧል።
- ውጣቱ ራሱንና ሌሎችን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በመከላከል ስራ ፈጣሪ ሆኖና አርአያነቱን የሚያሳይበት ምቹ ሁኔታም ሆነ ውስጣዊ ተነሳሽነት ሊኖረው አልቻለም።
- ወላጆች ፣ ፈፃሚ አካለትና ሌሎች ሀይሎች እነዚህን ተቋማት ተቀናጅተው ለመቀጠል/ለመሰራት ተስኗቸዋል። ለማበታታት ለማገዝም ሆነ

ልንቀበለው የሚገባን እውነት

- በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ከመከላከልና መቆጣጠሩ አንፃር የእድሮች፣ ወጣት ክበባት፣ የጎሳ የባህል ቡድኖች፣ የመረጃ ማህበሮች ወዘተ የሚኖራቸው ሚና በማንም የማይተካ ነው፡፡
- እነዚህ ተቋማት የተቋማቱ መሪዎች በሚወክሉት ህ/ሰብ ባላቸው ሰፊ ተቀባይነትና ተሰሚነት ሳቢያ አጠቃላዩን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ውጤታማነት ሊያፋጥኑ የተፈለገውን መረጃና መልዕክት በቀላሉ ወደ ታላሚ ሊያደርሱ የህ/ሰቡን እውነተኛና ተቀዳሚ እግር ከስር ፈንቅለው አካባቢያዊ ዘላቂ መፈትሄ ሊያበጁ ፣ ያንንም በሚገባ ሊያስፈጽሙ ይችላሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የሚደረገውን ዙሪያ መለስ ጥረት ሊያሽመደምዱ የተሳሳተ አቅጣጫ ሊያሳዩ የሚችሉ ናቸው፡፡
- በትክክል አሁን በእያንዳንዱ ቦታዎች እንዳየነው በተለይ እድሮች ከተባበሩ ተዓምር መፍጠር እንደሚችሉ ፍንጭ ሰጥቷል፡፡ አንዳንድ አካላትም በተለይ ለኤድስ ህሙማን ፣ ለወላጅ አልባ ህፃናት ፣ ለአረጋዊያን፣.. ተገቢውን ዘላቂ ድጋፍና እንክብካቤ ለመስጠት የሴቶችን የህፃናትንና፣ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋረ የሚኖሩ ወገኖችን መብቶቸ ለማስከበርም ሆነ በልማት እንቅፋት የሆኑ ማህበራዊና ጎጂ ልማዶች ለመቅረፍ፣ ህብረተሰቡን በስፋት ለማንቀሳስ፣ ወዘተ እነዚህ ማ/ሰባዊ ተቋማት እጅግ ወሳኝ መሆናቸውን በመቀበል አብረው ለመሰራት ፍላጎት እያሳዩ ነው፡፡
- በእርግጥ እነዚህ ተቋማት ለዘመናት ሲያራምዱት ከነበረው አስተሳሰብ እና ከዘመናዊ አሰራር ጋር ለመተዋወቅ ከነበራቸው እጅግ አናሳ እድል በመነጨ የተሳሳቱ አመለካከቶች፣ የአቅም ማነስ፣ የአደረጃጀት ችግሮች አሉባቸው፡፡ ይህ ግን አያስደንቅም መታወቅ ያለበት ከቀረብናቸው እድሉን ካገኙ ፣ ድጋፋችንን ከሰጠናቸው ፣ የራሳችን ፍላጎት ለመጫን ሳይሆን የእነሱንም ሀሳብ አዳምጠን አብረን መስራት ከቻልን የእነዚህን ተቋማት አቅም መገንባት በሚፈለገው ገንቢ እቅጣጫ እንዲጓዙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ተችሏልም፡፡
- መታወቅ ያለበት ዋነኛው እውነታ ፣ ማንኛውም የልማት ችግሮቻችን ለመፈታት የሚያስችል አቅም እነዚህ ተቋማት ጋ መኖሩን ካለነዚህ ተቋማት የነቃ ተሳትፎ ጥረታችን ከግብ ሊደርስ እንደማይችል አብሮና ተመካክሮ በመስራት ሁሉንም ነገር መለወጥና ጠቃሚ ማድረግ የሚቻልም ግዴታም መሆኑን ነው፡፡
- በአላባ የታየው ውጤታማ የማህበረሰብ ውይይት ስራ ፣ በጉራጌ የተስተዋለው ሰፊ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ የደም ምርመራ እንቅስቃሴ ወዘተ ካለ እነዚህ ተቋማተ የነቃ ተሳትፎ ግቡን ይመታ ነበር ማለት እውነታን መካድ ይሆናል፡፡

*ሠ. አትራፊ የልማት ተቋማት*

ውጫዊ አመለካከት

- ብዙዎች እነዚህን የልማት ተቋማት /ፋብሪካዎች፣ ሰፋፊ እርሻዎች የኮንስትራክሽን ጣቢያዎች፣ ማዕድን ማምረቻዎች ወዘተ/ ከአካባቢው የህ/ሰብ ህይወት ነጥለው ያዩዋቸዋል፡፡ በተቋማቱና በዙሪያቸው ያለው የገጠርና የከተማ ህይወት መካከል ቁርጠኝነት እንደሌለ ይቆጠራል፡፡

- በተቋማቱ መኖር፣ አሰራር፣ ይዞታ ፣.. እና በልማት ፣ በማህበራዊ ቀውስ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ያለውን ትስስር ያለመቀበል አስተሳሰብ አለ፡፡
- ትርፋማ እስከሆኑ፣ ኢንቨስትመንት እስኪስፋፉ፣ ለውጭና ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሎ ምርቶችን እስካስገኙ፣ በርካታ ስራ አጦችን ቁጥር እስከቀነሱ ለአገር ልማት የሚበጅ መሰረተ ልማቶችን እስኪስፋፉ... እነዚህ የልማት ተቋማት ጥቅም እንጂ ጉዳት የላቸውም የሚል አመለካከት አለ፡፡
- በእነዚህ ተቋማት የውስጥ ስራ ገብቶ እንዲህ አድርጉ .. በማለት የምንከተለውን የነፃ ገበያ ሰርዓት መፃረር ተደርጎ ይታያል፡፡ በዚህ በኩል ነፃ ገበያ ትርፋማነት እያልን በሌላ በኩል ተፅዕኖ ማድረግ አይችልም የሚል
- ተቋማቱ ለራሳቸው ትርፍ የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እስከሆኑ እነዚህ ተቋማት ኤች አይ ቪ/ኤድስን እንዲከላከልና እንዲቆጣጠሩ ድጋፍ ማድረግ እንደማይገባ ፣ በአካባቢያቸው ማህበራዊና የልማት ችግሮችም ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት ተገቢ እንዳልሆነ ፣ ራሳቸው የቻሉና በነፃ የሚንቀሳቀሱ እስከሆኑ ሁሉም ነገር የራሳቸው ጉዳይ እንጂ ሌላውን እንደማመለከት ወዘተ አይነት አቋሞች አስተሳሰቦች ይንፀባረቃሉ፡፡
- እነዚህ ተቋማት ዛሬ ከሚያስገኙት ጥቅምና ትርፍ ነገና ከዚያ ወዲያ በማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች በተለይም በኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት አልያም መቀረፍ ዙሪያ የሚኖራቸውን እንድምታ በሌላ በኩልም እነዚህ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች በተቋማቱ ትርፋማነትና ህልውና ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተፅዕኖ አርቆ ያለማስተዋል ጉዳይ አለ፡፡

## ውስጣዊ አመለካከቶች

- ተቋማቱ በራሳቸው "የእኛ ተልዕኮ ትርፋማ መሆን፣ሸቀጣሸቀጦችን ማምረት፣ መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት፣ ስራ አጥነትን መቅረፍ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ስለሌላ ጉዳይ ማሰብ አይገባም" የሚል አመለካከት አላቸው፡፡
- በተቋሙ ውስጥ በሚከናወነው የኢኮኖሚና የስራ እንቅስቃሴ ውጪ በተቋሙ ዙሪያ ፣ በትክክል፣ በአገር ፣ ወዘተ ስላለው ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ፖለቲካዊ.. ጉዳይ ትኩረት መስጠት አላስፈላጊ ተደርጎ ይታያል፡፡
- ዛሬ ትርፋማ የሆነ ተቋም ፣ ወደፊትም እንደዚሁ እንደሚቀጥል ይታሰባል፡፡
- በተለይ ከከተማ ውጪ በሚቋቋሙ ተቋማት ዙሪያ የሚስፋፉት የወሲብና የመጠጥ ንግዶች፣ የሚፈናቀሉ ህዝቦች ፣ የሚፈጠሩ የባህልና ማህበራዊ ሁኔታ መደበላለቆች፣ ወዘተ ከተቋሙ ህልውና ጋር ቁርጠኝነት እንደማይኖረው ይታሰባል፡፡
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ለተቋማቱ ማውራት ስራ እንደመፍታት፣ የማይገናኙ ሁለት ነገሮችን ማገናኘት፣ የተቋማቱን ትርፋማነት ማጨናገፍ ከተቋሙ ተልዕኮና ተግባራት ውጪ የሆነ ጉዳይን እንደማንሳት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

## <u>አስተሳሰቡ የፈጠረው ክፍተት</u>

- እስከአሁን እነዚህ ተቋማት ተገቢውን ትኩረት እንዳይሰጣቸው፣ በእነዚህ ተቋማትና በዙሪያቸው መኖር ያለበት ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር ስራዎች እንዳይኖሩ ካሉም እንዳይጠናከሩና ባለቤት እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡
- ሌሎች አጋር አካላትና ተቋማቱ አብረው እንዳይሰሩ፣ ሰራተኛው ቤተሰቡና ማ/ሰቡ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ አደጋዎች ተገቢውን ጥበቃ እንዳያገኙ በአጠ

ቃላይ የስራ ቦታዎች የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ/ Work place HIV/AIDS Intervention/ እውን እንዳይሆን ምክንያት ሆኗል::

- ተቋማቱም ሆነ የመንግስት አካላት ለጉዳዩ ትኩረት እንዲነፈጉ በኤች አይ ቪ/ኤድስና በተቋማቱ ህልውና ዙሪያ ያለውን አሉታዊ ቁርጠኝነት እንዳይገነዘቡ አድርጓል::
- በተቋማቱ የሚያገለግሉ ሰራተኞች ቤተሰቦቻቸውና የአካባቢው ህ/ሰብ ማግኘት የሚገባውን ድጋፍና እንክብካቤ ፣ የህክምና የምክር አገልግሎት፣ የገንዛቤና ክህሎት ማደበሪያ ትምህርቶች ወዘተ እንዲያጣ በር ከፍቷል::
- እንደነዚህ ያሉ ተቋማት በተመሰረቱባቸው አካባቢዎች በርካታ ዜጎች፣ ልምድና እውቀት ያካበቱ ባለሙያዎች፣ አምራች የሆኑ ወጣቶች፣ የሴተኛ አዳሪዎች፣ ወጣት የገጠርና የከተማ ልጃገረዶች ወዘተ በተለያየ አጋጣሚ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጋልጠዋል፣ ብዙዎቹ ሞተዋል ፣ ቤተሰባቸው ተበትኗል፣ ህፃናትና ሴቶችም ለጎዳና ህይወት ተዳርገዋል::
- በዚህም ሳቢያ ተቋማቱ ለሰራተኞቻቸው ህክምና፣ ቀብር ወዘተ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጡ ፣ በሰራተኞቻቸው ከስራ መቅረትና ሞት ሳቢያ ምርታማነታቸው እንዲቀንስ ከፍተኛ ልምድና ችሎታ ያላቸውን ወጣትና ወሳኝ ባለሙያዎቻቸውን እንዲያጡ ተገድደዋል:: አገርና ህዝብም በዚህ ሳቢያ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳቶች ተጠቂ እየሆኑ ነው::
- እስከአሁን በክልላችን ወስጥ ባሉ ፋብሪካዎች፣ ሰፋፊ እርሻዎች፣ የኮንስትራክሽን ጣቢያዎች፣ ወዘተ የሰራ ቦታዎች የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራ ያለመጀመሩም ሆነ ይህንን ያካተተ የኢንቨስተመንትና የስራ ቦታዎች ፖሊሲዎች ያለመውጣታቸው አመለካከቶች የፈጠሩት ችግር ይመስላል::

<u>ልንቀበለው የሚገባን እውነት ፣</u>

- ዛሬ ባለው ሁኔታ ኤቸ አይ ቪ/ኤድስ ከቀጠለ በቅርብ አመታት ውስጥ አብዛኛዎቹ የልማት ተቋማት የባለሙያና የሰው ሀይል ቀውስ ሲገጥማቸው ለከፍተኛ የጤናና የኢንሹራንስ ወጪ መጨመር ፣ ለምርት ማሽቆልቆል ሊዳርግና ወደ ኪሳራ ሊያመራ እንደሚችል በግልጽ የታወቀ ነው::
- በተለይ በሰው ጉልበት ላይ በተሰረተ ስራ ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች፣ የማዕድን ማምረቻዎች፣ የኮንስትራክሽን ጣቢያዎች፣ ሰፋፊ የቡናና የሻቅጠል እርሻዎች በኤች አይ ቪ/ኤድስ ሳቢያ ለከፍተኛ ኪሳራ ቀውስ ሊጋለጡ እንደሚችሉ መታሰብ አለበት:: አንደቦትስዋና ያሉት ኤቸ ይ ቪ/ኤድስ በከፍተኛ መጠን ከጎዳቸው አገራት ውስጥ ማምረቻዎች /የማዕድን/ያሉ ከአደጋው የተረፉት ምናልባትም ቴክኖሎጂ መር /ሜካናይዝድ /ዘዴን የሚጠቀሙ ወይም በሰው ሀይል ጉልበት ላይ ያልተመሰረቱ በመሆናቸው ነው::
- በዚህ ሁኔታ መፈጠር ደግሞ ተቋማቱ ብቻ ሳይሆኑ ሰራተኞቻቸውና ቤተሰቦቻቸው፣ በተቋማቱ ዙሪያ ያለው ህ/ሰብ፣ ከሁሉም በላይ የአገር ኢኮኖሚ ደህንነት አደጋ ውስጥ ሊወድቅ፣ ማህበራዊ ቀውስም / ለወላጅ አልባ ህፃናት ቁጥር መጨመር፣ የሰብአዊ መብት የቤተሰብ መበተንና መፈናቀል፣ ወዘተ/ ሊፈጠር የመቻሉን ሀቅ ሁሉም አካል ሊረዳው ይገባል::
- እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገራት ውሰጥ አንዳንድ የማዕድን ማምረቻ ከገጠ ማቸው ቀውስና አንዳንዶች ይህንኑ በመረዳት ሰራተኞቻቸው የART መድሀኒት በነፃ እንዲያገኙ /በቅርቡ በአገራችን የባቱ ቢራ ፋብሪካ

እንደወሰደው ውሳኔ/ ከተደረጉት እርምጃዎች መማር ጠቃሚ ነው:: በሀገራችን በቤንች ማጂ ፣ ከፋ ዞኖች ባሉ ሰፋፊ የቡናና ሻይ ልማት እርሻዎች፣ በግልገል ጊቤ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግንባታ ጣቢያዎች፣ በአዶላ የወርቅ ማምረቻ ተቋማት ወስጥና በዙሪያቸው የደረሱትን የከፉ ጉዳቶች ማጥናትና መማር የሁሉም ሃላፊነት ነው::

- በአሁኑ ሰዓት በአትራፊ የልማት ተቋማት ውስጥም በዙሪያቸው ተገቢውን የተጠናከረ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራ በጊዜ መጀመር፣ ከዚያም አልፎ በተቋማቱ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ እቀድ ውስጥ ጉዳዩ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ማደረጉ ለተቋሙም ፣ ለሰራተኛውም በዙሪያው ላሉ ህዝቦችም፣ ለአገርም የህልውና ጉዳይ ነው:: ሃላፊነቱም የአንዱን ወገን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም አካላት መሆን አለበት::
- ከአሁኑ ረጋ ብሎ ማሰብ ከተቻለ የነፃ ገበያውን መርህ በማይፃረር የህዝቦችን መብቶችም በማይጎዳ፣ ትርፋማነትንና ማግኘት የሚገባንን ዘላቂ ጥቅም በማያሳጣ .. ሁኔታ ተገቢውን የጋራ መከላከልና መቆጣጠር ስልት በመዘረጋት ችግሩን ከወዲሁ ማቆም ይቻላል::

## ረ. የግል ተቋማት /Private Organizations/

### ውጫዊ አመለካከት

- የግሉ ዘርፍ በማህበራዊና የልማት ተግባራት፣ የመንግስትና የህዝብ አጋር ሆኖ የመሰለፉን አግባብነት ያለማመን::
- የገሉ ዘርፍ ትርፍ ከማሳደድ ባሻገር ለሌላው የአካባበቢው ጉዳዮች ትኩረት አንደሌለው የመቁጠር
- የገሉ ዘርፍ በኤች አይ ቪ/ኤድስና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲሳተፍ ቢደረግ ያለውን ውሰን ሀብት ያለአግባብ ሊያባክን እንደሚችል የማሰብ፣
- የግሉ ዘርፍ ለንቅዘት፣ ለሙስና፣ ያለአግባብ ለመበልፀግ፣ ህ/ሰቡን ለመበዝበዝ፣ ወዘተ የቆመ እንጂ ህ/ሰቡን የማገልገል የህዝብና የመንግስት ጥሪት ለማገዝ ፍላጎትም ሆነ የሞራል ብቃቱ እንደሌለው የመደምደም፣ ከዚህ ዘርፍ ጋር የሚሰራ ማንኛውም የመንግስትም ሆነ ሌላ አካል ሁሉ የጥቅም ትስስር እንዳለው አደርጎ የመውሰድ
- ከግሉ ዘርፍ ጋር ተባብሮ ለመስራት፣ አስተማማኝ ያልሆነ ፣ በቂና አመቺ የሆነ አመለካከት ፣ የአሰራርና አደረጃጀት ብቃት የሌለው እንደሆነ አድርጎ የማየት:
- የግሉ ዘርፍ የህ/ሰቡ ችግር የማይመለከተው፣ የማይሰማው፣ .. ይህንን ለመቅረፍም ምንም አስተዋጽኦ እንደማኖረው የማመን እና መሰል አመለካከቶች የተለያዩ አካላት በግሉ ዘርፍ ላይ ከሚያንፀባርቋቸው ውሰጥ አንዳንዶቹ ናቸው::

### <u>ውስጣዊ አመለካከቶች</u>

- የግሉ ዘርፍ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ትርፍ እያገኘ ተገቢውን የመንግሰት ቀረጥ ከመክፈል ውጪ ሌላ ሀላፊነት እንደሌለው ቢኖረወም እድሉ እንዳልሰጠው፣

- በግሉ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችና በማህበራዊ ጉዳዮች / ለምሳሌ በኤች አይ ቪ/ኤድስ መካከል ምንም ቁርኝት እንደሌለው
- በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የተባለው ጉዳይ ትልቅ የውጭ እርዳታ ስላለው ቢቻል አጋጣሚውን ተጠቅሞ ትርፍ ማግኘት እንጂ ይባስ ብሎ የራስን ሀብት ለዚህ ጉዳይ ማዋል ፈጽሞ የማታሰብ እንደሆነ
- በአብዛኛው " ምን ቸገረኝነትና " የራሱ ጉዳይ!" የሚለው አመለካከት በሰፊው ይንፀባረቃል::

## አስተሳሰቡ የፈጠረው ክፍተት

- ከግሉ ዘርፍ ይገኝ የነበረው ወሳኝ ፣ ዘላቂና ሰፊ አቅም በአግባቡ ጥቅም ላይ አልዋለም::
- የግሉ ዘርፍና ሌላው አካል አብሮ ለመስራት፣ ለመቀራረብ እድል አላገኘም ::
- እንደውም በቂ ግንዛቤ ከማጣትና አንድምታውን ካለመረዳት የግሉ ዘርፍ ይባስ ብሎ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የማስፋፋት፣የሴቶችና ህፃናት መብቶች መጣስ፣ ወዘተ እንደባባስ የማድረግ ሁኔታዎች የሚታዮበት አጋጣሚ ይታያል::
- በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠሩ ረገድ መንግሰት ለግለሉ ዘርፍ በሰጠው እድል ዘርፉ በሚገባ ሊሳተፍ አልቻለም :: የክልሉ መንግስት በአዋጅ ለግሉ ዘርፍ የሰጠው ሃላፊነትም በሚገባ ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም ::
- ውሳኔ ሰጪዎችና የመንግስትና ሌሎች ተቋማት ሃላፊዎችም ተጠቃቂነትን ሊፈጠር የሚችል ሃሜትን በመፍራት ለግሉ ዘርፍ ተገቢውን ድጋፍ አድርጐ በመከላከልና መቆጣጠሩ ዘረፍ ተሳታፊ ለማድረግ ድፍረቱን እንዲያጡ አድርጓቸዋል::
- እስከ አሁን በክልላችን ኤች አይ ቪ/አድስን በመከላከልና መቆጣጠር ስራ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን አጋርነታቸውን ያሳዩ የግሉ ዘርፍ አባላት እጅግ ትንሽ ናቸው::
- የግሉን ዘርፍ ግንዛቤ ለማዳበር፣ስለ አዋጆች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች ለማሳወቅ፣የአፈፃፀም አቅሙን ለማሳደግ፣ የተደረጉት ጥረቶችም ይህን ያህል ናቸው :: ከአቅሙና አደረጃጀቱ ጋር የተጣጣመ ቀልጣፋ አሰራር ለመፍጠርም አልተሞከረም::
- የንግድ ምክር ቤቶች፣ባለብቶች ፣የኢንቨስትመንትና አገልግሎት ተቋማት ወዘተ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ተነሳሽነት ሊያሳዩ አልቻሉም::

## <u>ልንቀበለው የሚገባን እውነት</u>

- የግሉ ዘርፍ አሁን ካለው አጠቃላይ አሰራር አንፃር የተወሰነ የአቅምና አመቺነት ችግር ቢታይበትም ባለው አሰራር አደረጃጀት አቅም ለልማት አግዥ የመሆን ሚናውን ሊወጣ ይችላል:: ቀስበ ቀስም አቅሙን ማጎልበት አመቺ አስራር መፍጠር መተማመንን ማስፈን ወዘተ ይቻላል::
- ሌላው ቢቀር የግሉ ዘርፍ ያለውን ሃብትና አጋጣሚ ለዘላቂ የአገርና የህዝብ እድገት በሚበጅ መልኩ ማዋል ቢችል እንኳን በራሱ ድህነት ለመቅረፍና ማህበራዊ ችግሮችን ለማስወገድ አንዳች ጠቀሜታ ይሰጥ ነበር::
- በአሁኑ ስዓት በትምህርትና ስልጠና፣ በጤና፣ በመረጃ ስርጭት፣ በመዝናኛ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣በአገልግለቶች አቅርቦት ወዘተ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና አስትዋጽኦ ከመቸውም በላይ እያደገ ሂዷል:: ይህ መሰሉ ተሳትፎ ደግሞ የስራ

እድልን በመፍጠር ተጋላጭነትን በመቀነስ፣የመረጃ ልውውጥልን በመፍጠር ህ/ሰቡን የአገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ ወዘተ በራሱ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ጠቀሜታ አለው፡፡

- ሆኖም ግን የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ፣ጊዜናጉልበትን በዚህ መልኩ የሚያሰፋፋቸው አገልግሎቶችና መስረተ ለማቶች በአግባቡ ውጤታማ እንዲሆኑ መጀመሪያ ህልውናው የተጠበቀ፣ የኢኮኖሚና የግንዛቤ አቅሙን ያዳበረ ወዘተ ተጠቃሚ፣ የተረጋጋና የተመቻቸ ማ/ሰብ አስተማማኝና ዘላቂ ገበያ እንዲሁም በበቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል ያስፈልጋቸዋል፡፡ ኤች አይ ቪ/አድስ ደግሞ ይህንን ወሳኝ የኢኮኖሚ አቅም እያዳከመ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጥራል፡፡

በሌላ አባባል የግሉ ሴክተር ምርተማነትና ውጤታማነት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ሳቢያ አደጋውስጥ ይወድቃል፡፡ በሌላ በኩል የግሉ ዘርፍ የማህበረሰቡ አንድ አካል እንጂ የተለዩ አይደሉም፡፡

- በሌላ በኩል የግሉ ዘርፍ የማ/ሰቡ አንድ አካል እንጂ የተለዩ አይደሉም ማ/ሰቡ የሚጐዱ ነገሮች ሁሉ የግሉንም ሴክተር መጉዳታቸው አይቀርም፡፡ የተገልጋዩ ህብረተሰብ አቅም በተጠናከረ ቁጥር ደግሞ የግሉ ሴክተር ውጤታማነትም አብሮ ያድጋል፡፡
- የግሉ ዘርፍ የህ/ሰቡ አካል ነው ከተባለ ለሴክተሩ ህልውና ሆነ ሴክተሩ ላለበት ህ/ሰብ ሁለንተናዊ ደህንነት በንቃት የመሳተፍ፣ባለው አቅም ሁሉ የመንግስትንና የሌሎች የልማትና ማህበራዊ አካላት ጥረቶችትን በአጋርነት የሚደገፍ የዜግነትና ሰብአዊ ሃላፊነት አለባቸው፡፡
- በተለይ የግሉ ተቋም ከተሰማራበት ዘርፍ ጋር በተቆራኘ በርካታ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላል፡፡
- የግሉ ዘርፍ ከሌላው የህ/ሰብ አካል ጋር ሲነፃፀር ይነስም ይብዛ የተሻለ የኢኮኖሚ እና የአቅም ደረጃ አለዉ ፡፡ እድልና አጋጣሚውም አላቸው፡፡

<u>ለምሳሌ</u> ሃብቱን ለዘላቂ የሀገርና የህ/ሰብ እድገት በሚበጅ የኢንቬስትመንት ዘርፎች ቢያውል ለራሱ አንድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

የሆቴል ባለቤቶች ኮንዶምን ለተጠቃሚው በማቅረብ በሴት ሰራተኞቻቸው ላይ ወሲባዋ ጥቃት እንዳይደርስ እራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ተገቢዉን የህክምናና ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ፣የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሆቴል ባለቤቶች ላይ የሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ የለም፡፡ ወይም በጣም ትንሽ ነው ፡፡ ጥቅሙ ግን ያጎላ ነው፡፡ የግሉ ሴክተር ጠቃሚ አጋር ይሆን ዘንድ የአሪቱም ይሁን የክልላችን መንግስት ሁኔታውን ምቹ አድርገዋል አሰራርም ተዘርግቷል በሩ ተከፍቷል፡፡ የግል ት/ቤቶችና ማሰልጠኛ ተቋማት ወጣቶች፣ ወዘተ የትምህርት እድል እንዲያገኙ፣ የስራ እድል ፈጣሪ እንዲሆኑ ወዘተ ማድረግ በተጨማሪም በተቋሙ የሚገኙ ተማሪዎችና ስራተኞች ራሳቸውን በሰነ መግባር እንዲናንፁ፣ ከአች አየ ቪ/ኤድስ ራሳቸውን እንዲጠብሪቀ፣ የጠና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣ በመከላከሉና መቆጣጠሩ ዙሪያ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ፣ በማበረታት በመደገፍ ከሌሎች አጋሮች ጋር ተባበሮ በመስራት ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አላቸው አጋጣሚውም ይፈቅድላቸዋል፡፡

ነጋዴዎች ህብረት ፈጥረው ከሚያገኙት ትርፍ በየወሩ በያዋጡ በርካታ ተጐጂ ወገኖችን ለማዳንና ለማሳደግ የሚችል ስራ ለመስራት የሚያስችል እገዛ ያደርጋሉ፡፡በለላ በኩል የግሉ ሴክተር ለትርፍ ማግኛነት የሚያካሂዱት ተግባራት ኤች አይ ቪ/ኤድስ የማያስፋፉ መሆናቸውን የማረጋገጥ አዋጅ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

### 4.1.3 መንግሥታዊ ባልሆኑ ሁሉም አካላት ዙሪያ መፈጠር ያለበት አመለካከት

*ቀደም ሲል በሰባት ንዑሳን ዘርፍ ለማየት በሞከርናቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ዙሪያ በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ወቅታዊ ያቂ አንፃር የትኛውም አካል ሊይዘው የሚገባ ወሳኝ አመለካከት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ ተጠ ቅሷል።*

- *ኤች አይ ቪ/ኤድስ የጤና ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ ልማት ችግር ነው። ኤች አይ ቪ/ኤድስን ዘንግተን የምናካሂደው የትኛውም የልማት ስራ የተጠ በቀውን ውጤት አያመጣም።*
- *ኤች አይ ቪ/ኤድስ የግለሰብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጠቃላዩ ማህበረሰብ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ኤች አይ ቪ/ኤድስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእያንዳንዱ የህ/ሰብ ክፍል ህልውና ላይ አደጋ አለው።*
- *ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ለየትኛውም አንድ አካል የሚተው አይደለም። ሁሉም የህ/ሰብ ክፍል ከዚህ አንፃር የራሱ ድርሻ አለው። በመሆኑም የእያንዳንዱ አካል ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ሊበረታተታ ሊደገፍ ይገባዋል።*
- *ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ስራ የምንካፈለው ሌላ ወገንን ለመጥቀም ብቻ አይደለም። ለእያንዳችን በተለይም ለምንኖርባት ሀገርና ህዝብ/ እኛን ጨምሮ/ እድገት፣ ድህንነትና ፈጣን ልማት ስንል ነው።*
- *እያንዳንዱ አካል በተሰማራበት ዘርፍ የሚገባውን ስራ ጠንክሮ ከሰራና ሀላፊነቱን በአግባቡ ከተወጣ እንኳን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መቀልበስ አስተዋፅኦ አለው።*
- *ድህነት፣ የሴቶች ጭቆናና ቃት ፣ የፍትህ መዛባት ፣ ሙስናና ንቅዘት፣ የትምህርት፣ የጤናና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ያለመስፋፋት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ስራ አጥነትና፣ ለኤድስ መስፋፋት አስተዋፅኦ አለው። እነኚህን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጠንቆች መዋጋት ኤች አይ ቪ/ኤድስን መዋጋት ነው።*
- *ሁሉም በየዘርፉ ባለው መልካም አጋጣሚ የመፈጸም አቅም ላይ ተመስርቶ የበኩሉን በማድረግ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ተገቢውን ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። ቢያንስ ኤች አይ ቪን የሚያስፋፉ ተግባራትንና አሰራሮችን በመቀየር ድርሻውን ይወጣል። ሆኖም ግን ሁሉም ፈፃሚ አካል ሁሉንም ነገር በአንዴ ሊፈጽመው አይችልም። ሁሉም የየራሱ የተለየ አማራጭና ድርሻ አለው።*
- *አለባብሶ በማረስ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በዘላቂነት መዋጋት አይቻልም። የችግሩን ስር መሰረት አግኝቶ መንቀል መቻል አለበት።*
- *ከሌላ አገራት ጋር ሲነፃፀር በአገራችን መንግስታዊ ያልሆኑ ፈፃሚ አካላት በተሳትፎ፣ በብዛት፣ በስርጭትም ሆነ በልምድና በአቅም ገና ብዙ ይቀራቸዋል። የእነዚህን አካላት አቅም ማጠናከር ኤች አይ ቪ/ኤድስንና ደህነትን መዋጋት ነወና።*
- *ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚሻው ምላሽ ዘርፈ ብዙ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ እንደሁኔታው ተለዋዋጭ* /Flexible/ ፣ *እየተገበርን የምንማረው፣ ሰፊ ሽፋን የሚጠይቅ፣ ሁሉንም ያሳተፈ መሆን አለበት።*

- ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ውጤታማ የመከላከልና መቆጣጠር ስራው ወሳኝ የሆነው ራሱ የችግሩ ተጠቂ ነው:: መፍትሄው ያለው የችግሩ ገፈት ቀማሽ ክፍል ጋ ነው::
- ከሌላ ቦታ የመጣ መፍትሄ አንድ ሌላ አካባቢ ችግር መንገድ ያሳይ እንደሆን እንጂ ፍፁም መፍትሄ አይሆንም::
- ስለዚህ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ከብሮሸርና ፖስተር ማዘጋጀት፣ ወርክሾፕ ከመስጠት፣ ከድራማና ዘፈን.. በላይ የጠለቀ ፣ ማሰብን፣ ወደ ህ/ሰቡ መውረድን፣ የችግሩን ምንጭ መፈተሽን፣ ለእያንዳንዱ የተለየ አካባቢ፣ የህ/ሰብ ክፍል፣ ሁኔታና የችግር ጥልቀት ፣ የየራሱ የሆነ የተለየ መፈትሄ ያሻዋል::
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን በውጤታማነት ለመከላከልና መቆጣጠር ዋነኛውና ወሳኙ አቅም ያለው ህ/ሰቡ ራሱ ጋ ነው:: ይህ እምቅ አቅም የሚወጣውና ውጤት የሚያስገኘው ግን ወደዚያ ህ/ሰብ ዘልቀን፣ አብረን ቁጭ ብለን፣ ስናማክረው፣ስንሰማው፣ስናበረታታው፣እምነቱን፣ሀሳቡን፣ ተሞክሮውን፣ስሜቱን ተቀብለን "እናስ ምን ይሻላል?" ስንለው ብቻ ነው:: ይህንን ለማድረግ የሚያስችለን ብቸኛ መሳሪያ ግን "የማህበረሰብ ውይይት" /**Community conversation /** ነው::
- በማህበረሰብ ውይይት፣ የህ/ሰቡን እውነተኛ ችግርና ፍላጎት፣መፍትሄና አቅጣጫ፣ አወቀን አብረነው ስናቅድ፣ ሰንፈጽም፣ ችግራችንን ስንገመግም፣ ስንማማር የዚያን ህዝብ ራሱን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመከላከልም ሆነ ፣ የችግሩን ቁስል ለማገገም የሚያስችለውን እውነተኛና ዘላቂ አቅም እናስታጥቀዋለን:: ከዚያም እኛ አናስፈልግም:: ፈንድም አያስፈልግም:: ሁሉም እዚያ ህ/ሰቡ ጋ አለና!
- ስለዚህ መንግስታዊ ያልሆኑም ሆነ የሆኑ አካላት /ድርጅቶች/ ዋነኛ ተልዕኮ በዚህ መልኩ የችግሩን ተጠቂ ህ/ሰብ አቅም አጎልብቶ የራሱን ችግር ራሱ እንዲፈታ ማድረግ ነው:: አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው:: የችግሩም የመፈትሄውም የስራውም ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው:: ህ/ሰቡ የማይችለውን ስራ አብረው እየሰሩ ህ/ሰቡ ስራውን ሲችለው ወደ ሌላ ስራ መሸጋገር ፣ በዚህ ሂደት መቀጠል ነው::
- ሁሉም ደሀ በሆነበት አገር ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ስለሚኖር ብቻ በየወሩ ቀለብ መስፈር፣ ብር ማደል፣.. በኤድስ ሳቢያ ወላጅ አልባ ስለሆነ ብቻ አንሶላ፣ ብርድ ልብስ፣ ቆዳ ጫማ፣.. እየገዙ ማደል ውጤቱ ዘላቂ መፍትሄ ሳይሆን ጥገኝነትንና ጠባቂነትን ማስፋፋት ነው:: ጎረቤቱስ ያለው ወላጆቹ እያሉ የሚለብሰው ፣ የሚጎርሰው ያጣው ህፃን? ምነው የእኔም ወላጆች በኤደሰ ሳቢያ በሞቱ" ብሎ መመኘት አለበት?
- የምናደርገው ድጋፍና እንክብካቤ ተገቢውን ሰው የለየ፣ጥገኝነትን የማይፈጥር፣ ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ፣ ስብእናን የማይጎዳ፣ በሌሎች ዘንድ አፍራሽ የሆነ ሰሜትና አመለካከትን የማያስከትክ መሆኑን ቀድመን መመርመር አለብን::
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና መቆጣጠር ስንሰማራ መጓዝ ያለብን መንገዱን ስለቀለለን፣ አልያ ሌላ ጉዳያችን አማራጭ ስለሆነን መሆን የለበትም::
- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ድንበር አያውቅም:: እጅግ ሲበዛ ተንቀሳቃሽ ነው:: በጊዜና በቦታ አይወሰንም:: ዛሬ አንዱ ጋር የተፈጠረው ሁኔታ ነገ በጣም ሩቅ በሆነ ሌላ ቦታ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሊያባብስ፣ የፅዕኖውን ሊያጠነክር ይችላል:: እንደ አዋሳ ሀይቅ ውሀ ነው:: ሀይቁ እየሞላ ቢሄድ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ገድበን ከውሀ መጥለቅለቅ እንድናለን ወይ? ከጫፍ እስከ

ጫፍ መገደብ አለበት:: በአንድ አቅጣጫ እንኳን ትንሽ ቀዳዳ ቢያገኝ ውሀው ከመፍሰስ አይቆምም::

- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለዘለቄታው ለማቆምም መስራት ያለበት በሁሉም ዘርፍ፣ በሁሉም አካባቢ፣ በሁሉም አካል፣.. መሆን አለበት አንዱ ወረዳ ምን ያህል ምርጥ ስራ ቢሰራ፣ ጎረቤት ያለው ወረዳ ካልሰራ ውጤት የለውም፣ የደቡብ ክልል ምን ተዓምር ቢፈጥር፣ ኦሮሚያ ፣ ጋምቤላ ስራው ደካማ ከሆነ ከአደጋው አልተረፍንም::
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ችግር ያለው ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ገጠርም ነው:: አስፋልት ዳር ብቻ ሳይሆን ጉራንጉሩን ተሻገሮ አለ:: አዋሳና ሆሳዕና ላይ ብቻ ሳይሆን ኮንታና ሀመር ውስጥም አለ::
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ቅንጅት ይፈልጋል:: በቅንጅት አቅም ይፈጠራል በቅንጅት ዘርፈ ብዙው ምላሽ እውን ይሆናል በቅንጅት የአንዱ ክፍተት በሌላው ይሞላል:: አንዱ ብቻውን ግንበኛም፣ አናፂም፣ ጭቃ መራጊም፣ መሀንዲስም፣ .. ሊሆን አይችልም:: ግንበኛው፣ አናፂው፣ ጭቃ መራጊው፣ የቧንቧ ሰራተኛው ኤሌክትሪሺያኑ ሁሉም ተቀናጅተው በየሙያቸው ጠንክረው ከሰሩ ዘላቂ እውነተኛ ህንፃ ይገነባሉ:: ሁሉም ደግሞ የየራሳቸው ፕላን /ንድፍ/ አዘጋጅተው ሊሰሩ አይችሉም:: አንደ ህንፃ ያስፈልገናል፣ ስንት ክፍል፣ ምን ያህል ስፋት፣ ማቴሪያል፣.. ይወስኑና በመሀንዲሱ አማካኝነት ንድፉ ይዘጋጃል:: ከዚያም ሁሉም ባለሙያ የሚሰራው በዚህ ንደፍ ላይ ተንተርሶ ይሆናል::
- በኤች አይ ቪ/አድስ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ሀይሎችም በየራሳቸው አቅጣጫ፣ በፈቀዱት ስትራተጂ፣ .. መንቀሳቀሱ ውጤት አይኖረውም:: ሁሉም ለክልሉ ይበጃል ተብሎ ፈፃሚዎቹ ባሉበት በምክክር በተዘጋጀው የ 3 ዓመት ሰትራቴጂክ እቅድ ላይ ተመስርቶ መሰራት ይጠበቅበታል:: ወጥ የሆነ አሰራርም ያሻዋል:: መንግስታዊ ያልሆኑ ሀይሎች የመንግስት የልማት አጋሮች ናቸው:: የአጋርነት መገለጫው ደግሞ መንግስት የነደፈውን የድህነት ቅነሳ እስትራተጂ ፣ ያወጣውን መመሪያ ወዘተ.. በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ ከጎኑ መቆም ነው::
- እያንዳንዱ ፈፃሚ አካል ግልፀኝነት ፣ ተጠያነትና ተዓማኒነት ይጠበቅበታል:: የሚሰራው ለህዝብ ከሆነ ተጠያቂነቱም ለዚያ ለሚሰራለት ህዝብ መሆን አለበት:: ለህዝብ ያልታመነ፣ ለህዝብ ግልፅ ያልሆነ እንዴት ሩቅ ላለው ለጋሽ አካል /Donor/ ይታመናል?
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚንቀሳቀስ የትኛውም አካል ከቀበሌ እስከ ክልል ካሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ኮሚቴዎች ጋር ተቀራርቦ፣ ተደማምጦ፣ ተመካክሮ መስራት ስኬትና ቅንጅት ወሳኝ ነው:: የስራውን የየእለት ሂደትና ይዞታም በሪፖርት ማሳወቅ አለበት::
- ለጋሽ አካላትም ድጋፍ ያደረጉለት ፈፃሚ አካል ማንነት ፣ የድጋፍ መጠንና አላማ ለጽ/ቤቶች ማሳወቅ፣ የሚያደርጉት ድጋፍ ክልሉ በቀየሰው የ3 ዓመት ሰትራተጂክ እቅድ አቅጣጫ መሆኑን ማረጋገጥ የጋራ ውጤት ለማስመዝገብ ወሳኝ ነው::

## 4.1.4 አሰራር መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ዙሪያ

### ሀ. እስከ አሁን ያለው አሰራር

- ፕሮጀክት በአንድ አካባቢ ለመፈፀም የሚያቀርቡ መያዶች /በተለይ ከክልሉ ውጪ ባሉ ለጋሾች የሚደገፉ/ የቀረፁት ስራ ምን ያህል ተጠቃሚ ወገን ፍላጎትና ተሳትፎ እንደተንፀባረቀበት ምን ያህል በዚያ አካባቢ ያለውን እውነተኛ ክፍተት እንደሚሸፍን ምን ያህል በአካባቢው ካሉ ሌሎች ስራዎች ጋር የተቀናጀና ከክልሉ ስትራተጂክ ፕላን ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያረጋገጥ ግልጽ አሰራር አልነበረም፡፡

- እነዚህ ፈፃሚ አካላት በአዋጅ ስልጣኑ ከተሰጣቸው የክልል፣ የዞንና የወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ጋር ተቀራርበው እንዲሰሩ ፣ ወቅታዊ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ እንዲያደረጉ የስራቸውን ውጤታማነት በየጊዜው እንዲቃኙ የሚያስችል / አጠቃላይ ጽ/ቤቶቹ በአዋጅ የተሰጣቸው ሃላፊነት እንዲወጡ የሚያደርግ/ አሰራር የኦፕሬሽን ስምምነት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለመስራት የሚፈርሙት ከክልሉ የፋይናስ ኢኮኖሚና ልማት ቢሮና ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር ነው፡፡

- መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በሚፈፅሟቸው የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክቶች ዙሪያ በሚያገለግሉት ህ/ሰብ ተጠያቂነትና ግልጸኝነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ አሰራርም የለም፡፡

- በክልሉ በተለያዩ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ዙሪያ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲሰፍን አልተደረገም፡፡ ስለዚህ ለሰብሰባ ተሳታፊዎች የሚሰጥ አበል፣ ለበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የሚደረግ ማበረታቻ የሚሰጡ ስልጠ ናዎች የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎች የሪፖርት አቀራረብ፡ ወዘተ ወጥ አይደሉም፡፡
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ የሚከናወኑ ስራዎች ጥራት ፣ ብቃትና ተገቢነት የሚረጋገጥበትም ግልጽ አሰራር የለም፡፡ አፍራሽ መልዕክቶችን የሚያስራጩ፣ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት መንስኤ የሚሆኑ፣ መገለልና ጥላቻ የሚያባብሱ፣ የህ/ሰቡን ግንዛቤ የሚያዛቡ፣ ወዘተ አይነት ሁኔታዎች በብቃት ለመቆጣጠር የሚያመች ስልትና አሰራር አልተቀረፀም፡፡
- በፈፃሚ አካላት መካከል መቀራረብ ፈጥሮ ፣ እርስ በእርስ ለመማማር፣ መረጃ ለመለዋወጥ፣ በጋራ ጉዳይ ላይ የጋራ መፍትሄ ለመሻት የሚያስችል የመረጃ ልውውጥና የጋራ መድረክ ስርዓት አልተፈጠረም፡፡
- ምንም እንኳን በክልሉ አዋጅ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ማኛውም አካል በእለት ተዕለት ስራው ቢያንስ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ያለማስፋፋቱን፣ ቢቻል ደግሞ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና መቆጣጠር አስተዋጽኦ ማድረጉን ለማረጋገጥ ከዚህ አንፃር የተጠያቂነት አሰራር ለመፍጠር አልተቻለም፡፡
- መንግስታዊ ያልሆኑ ፈፃሚ አካላት የሚያቀርቧቸው የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በጣም በአጭር ጊዜ ተገቢውን ውሳኔ የሚያገኙበት ፈጣንና ቀልጣፋ አሰራር አልተዘረጋም፡፡እነዚህ አካላት ፕሮጀክት ጸድቆላቸው ድጋፍ ከተሰጣቸው በኋላ በተገቢው ወቅት ሪፖርት ካላቀረቡ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራርም የለም፡፡

- የፕሮጀክት ፈፃሚ አካላትም አቅምን በተለይ በሰው ሀይልና በማቴርያል በተፈለገ መጠን ለማጠናከር የሚቻልበት አሰራር የለም።
- መንግስታዊ ያልሆኑ ፈፃሚ አካላት በተለይ ሽፋን ባለገኙ ሩቅ አካባቢዎች /ደቡብ ኦሞ፣ ቤንች ማጂ፣ ዳውሮ ፣ / ሂደው እንዲሰሩ ለማበረታታት የሚያሰችል ልዩ ስርዓት የለም።
- የዞንና የወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ከራሳቸው የዞንና የወረዳ እውነታ አንፃር ከመያድ አካላት የሚቀርብ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን መርምረው አጽድቀው፣ የገንዘብ ድጋፍ አድርገው፣ ክትትልና ግምገማ እንዲያከናውኑ ሙሉ ሰልጣን የሚሰጥ አሰራር እስከአሁን አልነበረም።
- የተለያዩ የመንግስት አካላት፣ ለጋሾች፣ ወዘተ ከፈፃሚ አካላት እንዲቀረብላቸው የሚፈልጉት /የሚጠቀሙበት/ የፕሮፖዛል ማቅረቢያ፣ የሪፖረት ማድረጊያ፣ የገንዘብ ማስተላለፊያ፣.. ቅፆች /ፎርማቶች/፣ አካሄዶች፣ ሂደቶች፣ መስፈርቶች ወጥነት የሌላቸው የሚያምታቱ ሲሆኑ አንድ ወጥ የሆነ ክልላዊ አሰራርና ሁሉም የሚግባባበት አካሄድ እንዲኖር አልተደረገም።
- መንግስታዊ ባልሆኑ ፈፃሚ አካላት ዘንድ የጥናት ውጤቶችን፣ መረጃዎችን፣በብሄራዊና ክልል ደረጃ የተቀረፁ ጠቃሚ መርሆችንና የሚሰራጩ ጠቃሚ ልምዶችን በውሳኔ አሰጣጥ፣ በእቅድና ዝግጅት፣ ወዘተ የመጠቀም ልምድ የለም።
- በእነዚህ ፈፃሚ አካላት መካከል በእቅድ የሚመራ የአመራር ፣ የሰው ሀይልና የአስተገባበር አቅም ልማት ስርዓት አልተዘረጋም።

## ለ. የአሰራሮቹ ያለመኖር የፈጠረው ክፍተት

- ለመያድ አካላት በተለያዩ ለጋሾች የሚፅድቁና ድጋፍ የሚደረግላቸው ፕሮጀክቶች የህ/ሰቡን ፍላጎት ያላገናዘበ፣ ከክልሉ ስተራተጂክ እቅድ ጋር ያልተጣጣመ፣ የስራ ድግግሞሽ የሚፈጥር፣ በዚያ አካባቢ በሌሎች ከሚሰሩ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ጋር ወጥነት የሌለው። በዚህ ሳቢያም በተጠቃሚውና በፈፃሚ አካላቶቸ መካከል ግጭትና ያለመተማመን ያሰፈነ የሆነበት በርካታ አጋጣሚ ነበር።
- ፈፃሚ አካላት በተለያዩ የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች ምን እየሰሩ እንደሆኑ፣ እነማን እንደሆኑ፣ ከማንና ምን ያህል ድጋፍ እንዳገኙ፣ ምን ውጤት እንዳሰገኙ፣.. መረጃ ለማግኘት ችግር ፈጥሯል። ሪፖርት እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ የማይሆኑ በርካታ ናቸው። በዚህም የተነሳ የት ቦታ ምን ክፍተት እንዳለ ስለማታወቅ ከመረጃ እጥረት የስራ ድግግሞሽና የገንዘብ ብክነት የሚፈጠርበት ፍትሀዊ ሽፋን እንዳይኖርም መንስኤ የሆነበት ሁኔታ አለ።
- አንዳንድ ፈፃሚ አካላት ለአንድ ስራ ከተለያዩ ምንጮች ድጋፍ በማግኘት አለአግባብ ጥቅም ሲያገኙ የነበረበትና ስራቸው ምን ያህል የተፈለገውን መጠን ጥራትና ውጤት እንዳመጣ ለመገምገም ያልተቻለበት ሁኔታ አለ።
- የተለያዩ ፈፃሚ አካላት በሚሰሯቸው ተመሳሳይ ስራዎች በሚፈልጉት አይነት /Standard/ ስለሌለ እየሰሩ ውስን የሆነውን ሀብት ያለ ቅም ምሚያባክኑበት፣ ገንዘቡን ለግል ቅማቸው የሚያወሉበትም ሁኔታ አለ። በተለያዩ አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶችም ወጥ ያልሆኑ ስለሆኑ በአንድ ለማጠ ቃለልና ክልላዊ እይታውን ወይም የእያንዳንዱን ፈፃሚ አካል ውጤት በአንድ መስፈሪያ ለመለካት ችግር ፈጥሯል።

- አፍራሽ በሆኑ መልዕክቶችና ተግባራት ሳቢያ ህ/ሰቡ አላስፈላጊ ለሆነ ውዥንብር ፣ ስጋትና ፍራቻ፣ ለተሳሳተ ድምዳሜ ወዘተ የሚጋለጥበት ሁኔታ አለ። አንዳንዴ ለነዚህ ተግባራት የወጣው ገንዘብ፣ ጉልበትና ጊዜ ምንም ውጤት ሳያስገኝ ይቀራል።
- በፈፃሚ አካላት መካከል መማማር፣ መናበብ፣ ከአንዱ ተሞክሮ ሌላው ልምድ ቀስሞ የተሻለ ስራ ለመስራት ከላይ በተዘረዘሩት ችግሮች ላይ መክሮ የራሱን የጋራ መፍተሄ ለመውሰድ በጋራ መደጋገፍ አቅሙን እንዳያሳድግ የስራ ድግግሞሽ እንዳይፈጠር ለማድረግ እንዳይችል ሆኗል።
- መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በፈለገው ፍጥነት ውሳኔ እያገኙ በተቻለ መጠን ሰፊ ሽፋንና ስራ እንዲኖራቸው ለማድረግ አቅማቸውን በመገንባት የስራ ድርሻቸውን ቀልጣፋና የተጠናከረ እንዲሆን ለማስቻል ሁኔታዎች አልተመቻቹም። ፍጥነት ባለው መልኩ የተገኘው የፋይናንስ ድጋፍ ጥቅም ላይ እንዳይውል ሰበብ ሆኗል።
- ሩቅና ለስራ አስቸጋሪ የሆኑ የክልሉ በርካታ ወረዳዎች አሁንም በቂ ሽፋን ሳያገኙ ቀርተዋል።
- ዞኖችና ወረዳዎች የሚጠበቅባቸውን ስራ እየሰሩ ራሳቸውን እንዲያጠናክሩ እንዲሁም በርካታ የእለት የዕለት ስራዎች በክልል ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ላይ እንዲጫንና ስራዎች እንዲጓተቱ ምክንያት ሆኗል።
- ፈፃሚ አካላት ከተለያዩ ምንጮች ለተገኙ ፕሮጀክቶች ፣ ለተለያዩ አካላት ለሚቀረቡ መረጃዎች ፣ የተለያየና የየራሱ የሆነ ስራ በመስራት ጊዜ እንዳያባክኑ ሁሉም አካላት ወጥ የሆነ መረጃ እንዳያገኝና አንዱ ከሌላው ያለመግባባት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ የሀብት ብክነም አስከትሏል። ፈፃሚ አካላት የሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች፣ ፕሮፖዛሎች፣ ወዘተ የተምታቱ የሚሆኑበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

## ሐ. በዚህ የህዝብ ንቅናቄ የሚጠበቀው የአሰራር ለውጥ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ዙሪያ

### መንግስታዊ ያልሆኑ ፈፃሚ አካላት

- በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰሯቸው ስራዎች ከአቅድ እስከ ፍፃሜ ተጠቃሚውን ወገን በንቃት ያሳተፉ፣ ፈላጎቱን ያንፀባረቁ፣ ተቀዳሚ ችግሩን ለይተው ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኙ የክልሉን የ3ዓመት ስትራተጂክ ፕላን መሰረት ያደረጉ በብሄራዊና ክልላዊ ደረጃ የተቀመጡ አመልካቾች የሚመዘኑ /የሚለኩ/ ክልላዊውን መስፈርት የሚያሚሉ፣.. በአካባቢው ካሉ ሌሎች ፕሮጀክቶች /ስራዎች/ ጋር የተቀናጁ መሆናቸውን ያረጋገጣሉ።
- ከየተኛውም አካል በተገኘ ድጋፍ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የተያያዘ ስራ የሚሰሩ ቢሆኑም ከክልል፣ ዞንና ወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መካላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ጋር በመቀራረብ፣ የስራቸውን ዝርዝር፣ የፕሮጀክት በጀቱን መጠንና ምንጭ በግልጽ በማሳወቅ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ የሚጠበቅባቸውን ዝርዝር የስራ ሪፖርት በማቅረብ ተግባብተው ይሰራሉ።
- ለክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የሚያቀርቧቸው የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በተዘጋጀው የፕሮፐዛል ማቅረቢያ ፎርማት መሆኑን የሚጠብቁት የጥራትና ይዘት ደረጃቸውን መጠበቁት በዞንና ወረዳ አካላት ታይተው ድጋፍ ያገኙ መሆኑን ለጠ

ቀኗቸው ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኙና የሚያገለግሉትን ህ/ሰብ ሰብአዊ ክብር ፣ የስራ ተነሳሽነት ፣ እምነትና ጠቃሚ እሴት የማሸረሽሩ፣ እንዲሁም በሌሎች አለካላት የሚደገፉ ስራዎችን ያላካተቱና ከራሳቸው የመስራት አቅምና ተመራጭነት /Comparative advantage/ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

- በክልሉ ወይም በሚሰሩበት አካባቢ ከሚገኙ ሌሎች ፈፃሚ አካላት ጋር ቅንጅት ፈጥረው ተቀራርበው ይሰራሉ
- በሚሰሩት ስራ ሁሉ ለሴቶች፣ ለወጣቶች ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡
- ቀልጣፋ የሪፖርትና የመረጃ ልውውጥ እንዲፈጠረ ያደርጋሉ
- በክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፎረም በመሳተፍ በክልሉ ወጥ የሆነ ቀልጣፋ ሁሉን አቀፍ የሆነ አሰራር እንዲኖር ጥረት ያደርጋሉ
- ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና የሃላፊነት ስሜት ያለውን አሰራረ ያሰፍናሉ
- የክልሉ የ3 ዓመት ስተራተጂክ ፕላን ውጤታማ የሚሆንበት አሰራር እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- ልምዳቸውን ለሌሎች በማካፈል ፣ የሌሎችን ልምድ በመቀሰም በጎ ተሞክሮዎችን በማስራጨት፣.. የሁሉም አካላት ስራዎች ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ይጥራል፡፡
- የክልሉ ሁሉም የህ/ሰብ ክፍሎችና አካባቢዎች በተቻለ መጠን ፍትሀዊ ሽፋን የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፣
- ለጋሾቻቸውና ተባባሪዎቻቸው ከክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡
- የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤትም ሆነ ጽ/ቤት የሚያወጧቸውን መመሪያዎች፣ የሚያሰራጯቸውን መረጃዎች፣.. በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን መንገድ ይፈጥራል፡፡
- በምንም መንገድ የሚያከናወኑት የትኛውም ስራ ቢያንስ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የማያባብስ፡ መገለልና መድሎዎንና፣ ፍራቻን የማያጠናክር .. መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

## ተገልጋዩ ህብረተሰብና የመንግስት አካላት

- መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የሚተገብሯቸው ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል እና ህ/ሰቡ የወከለው የመንግስት አካል ፈፃሚ አካላቱ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ፣ ፍላጎታቸውንና ተሳተትፏቸውን ያረጋገጠ፣ ድግግሞሽን ያስወገደ ከሌሎች ስራዎች ጋር ቅንጅት የፈጠረ፣ ለተጠቃሚው ህ/ሰብ ዘላቂ ጥቅም የሚበጅ ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣሉ፣ ይከታተላሉ፣ እንዲሁም ግፊት ያደርጋሉ
- ፈፃሚ አካላት በዚህ መልኩ በየአካባቢው ሊፈጽሙት ለፈለጉት ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት ያበረክታሉ፣ ህ/ሰቡን በማስተባበር ለፕሮጀክቱ ውጤታማነት የሚበጅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ
- በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ግምገማ ይሳተፋሉ፣ ፕሮጀክቱ በተፈቀደለት እቅድ ጥራትና መጠን መሰረት እየተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

## የክልል፣ የዞንና የወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ስራ አመራር ቦርድ

- ሁሉም ፈፃሚ አካላት፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ፣ የመንግስት አካላት.. ዘንድ የተጠ ያቂነት ፣ ግልፀኝነትና ቀልጣፋ አሰራር እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል::
- በፈፃሚ አካላት የሚቀረቡ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ሌሎች ጠ ያቄዎች በጽ/ቤቱንና በገምጋሚ ቦርዱ በፍጥነት ታይተው በሰራ አመራር ቦርዱ ፈጣን ውሳኔ የሚያገኙበትን ቀልጣፋ አሰራር ይዘረጋል::
- የክልሉ አድቮኬሲና መረጃ ስራዎችን ራታቸው የተጠበቀ መሆኑ እንዲረጋገጥ እርምጃ ይወስዳል::
- በተለይ የብሄረሰብ ልማት ድርጅቶች ፣የሃይማኖት ተቋማትና የግሉ ዘርፍ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሰፋት እንዲንቀሳቀስ የሚበረታታበትን አሰራር ያስፍናል::
- በክልሉ ወጥ የተቀናጀ አሰራር እንዲፈጠር ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፣
- መያድ አካላት እስከ አሁን ሽፋን ባላገኙ የክልሉ አካባቢዎች ሄደው እንዲሰሩ ልዩ ልዩ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የዞንና የወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች በሚገባ ተጠናክረው የመያድ አካላትን ስራዎች የሚከታተሉበትና የሚገመግሙበት አሰራር እንዲፈጠር ያደርጋል ፣
- ከዚህ በፊት የነበሩ የአሰራርና አፈፃፀም ችግሮች እየመረመረ አመቺና አሰፈላጊ የሆኑ አዳዲስና የተሻሉ አሰራሮች እንዲፈጠሩ ተገቢውን መመሪያ ያወጣል፣አፈፃፀማቸውም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል::
- ከክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮና ከክልሉ ጠ ₋ና ቢሮ ጋር በመነጋገር ፕሮጀት ፈፀሚዎች በሚፈርሙት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፕሮጀክቶች የክልሉ ኤች አይ ቪ/አድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በጣምራ እንዲፈርም ሁኔታዎችን ያመቻቻል::
- የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የአሰራር አደረጃጀት የሰው ሃይልና የቁሳቁስ አቅም የሚጠናከርበትን ቀልጣፋ ፣ ዘመናዊ፣ ፈጣን የሆነ አሰራር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል::

## የክልልና በየእርከኑ ያለ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች

- በክልሉ የተቀናጀ፣ ወጥ፣ ህብረተሰቡን መሰረት ያደረጉ፣ ዘርፈ ብዙ የሆነና ተጠያቂነተና ግክፅነት ያለው የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠር ሰራዎች መከናወናቸወ የሚረጋገጥበት ውጤታማ አሰራር በሚፈጠርበት ሁኔታ ለክልሉ ስራ አመራረ ቦርድ ሀሳብ ያቀረባል፣ ያስፈጽማል፣

- በክልሉ ቀልጣፋ ፣ ከክልሉ የ3 ዓመት ስተራተጂክ ፐላ ጋር የተጣጣመ ሁሉንም ወገን ያሳተፉ ፕሮጀክቶች በስፋት የሚከናወኑበትን ምቹ አሰራር ይፈጥራል፡፡
- በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ፈፃሚ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ፣ ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ፣ ለክልሉ የመከላከል ስራ ውጤታማነት በጋራ የሚመክሩበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ በክልሉ የኤች አይ ቪ/አድስ መከላከልና መቆጣጠር እቅድ ዝግጅት፣ በተከናወኑ ተግባራት ግምገማ ፣ በውሳኔዎች ወዘተ እንዲሳተፉ ያደርጋል፣ ስለ ክልሉ ስለ ክልሉ አጠቃላይ የመከላከልና መቆጣጠር ስራ በቂ መረጃ ያሰባስባል፣ ለተጠቃሚው ወገን ያሰራጫል፣
- ከለጋሽ አካላት ጋር በቀረብ በመፈራት ለፈፃሚ አካላት በቂ የገንዘብ፣ የቴክኒክና ማቴሪያል ድጋፍ የሚበቃበትን መንገድ ያመቻቻል፣
- በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ፈፃሚ አካላትን የቴክኒክና የአፈፃፀም ብቃት ለማዳበር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ሰልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ የቴክኒክና የማቴሪያል የበጀት ድጋፍ በማድረግ የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፣
- ከሚመለከታቸው የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመነጋገር፣ የዞንና ወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች በበቂ የሰው ሀይል፣ የማቴሪያል፣ የቴክኒክና በጀት አቀም መጠናከራቸውን ያረጋግጣል፣
- በክልሉ የኤድስ ስራ አመራር ቦርድና በኤድስ ም/ቤቱ የሚተላለፉና የሚወጡ ወሳኔዎች፣ መመሪያና የአሰራር ደንቦች ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
- የክልል፣ ወረዳና ዞን ለሴክሪታሪት ለፈፃሚ አካላት ቀልጣፋ፣ ፍትሀዊ፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለው አገልግሎት የሚሰጡበትን አሰራር ይመሰርታል፣ ተፈፃሚ ያደርጋል
- የመንግስትና መንግስታዊ

### ለጋሽ አካላት

- በክልሉ እንዲፈጽሙ የሚሰጧቸው ድጋፎች ፣የክልሉን ፍላጎትና የ3 አመቱን ስትራቴጀክ ፕላን ያገናዘቡ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፣
- ስለሰጧቸው ድጋፎች የተሟላ መረጃ ለክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ያሳውቃሉ፡፡
- ከጽ/ቤቱ ጋር ተቀራርበው ይሰራሉ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋሉ
- በክልሉ አንድ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲሰፍን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ

- ድጋፍ የሰጧቸው ፈፃሚ አካላት ከክልል ዞንና ወረዳ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ጋር ተቀራርበው እንዲሰሩ ያበረታታሉ ወቅታ ዊ የስራ አፈፃፀም ሪፓርት እንዲያቀርቡም ግፊት ያደርጋሉ የጽ/ቤቶቹንና የፈፃሚ አካላትን አቅም ያጠናክራሉ፣